
# የኦሮሞ እና የአማራ

## እውነተኛው የዘር ምንጭ

በፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ ጂግሳ



የሸፋን ስዕል፡- የጥንት ኦሮሞና አማራ ጠቢባን የፃፉባቸው ጥንታዊ ፊደሎች።





**ማውጫ** **ገጽ**


ስለደራሲው አጭር መረጃ 5

መቅድም 7

## ክፍል አንድ

## ኦሮሞ ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ ያበረከተው አስተዋጽኦ..............................15

ስነ-ልሳናዊ አስተዋጽኦ................................17

ፍልስፍናዊ አስተዋጽኦ................................20

መንፈሳዊ አስተዋጽኦ...................................23

ለውትድርና ጥበብ አስተዋጽኦ.........................26

ለትምህርት እና ለቅኔ/የግዕዝ ስነ-ቃል

ለግጥም የተደረገ አስተዋጽኦ...........................29

ለዳንኪራ እና ለ ሙዚቃ የተደረገ አስተዋጽኦ-----.30

የሙዚቃ መሳሪያዎችን በተመለከተ..................30

ልዩ ልዩ አስተዋጽኦዎች...............................31

## ክፍል ሁለት

**የኦሮሞና የአማራ ሕዝብ እውነተኛው የዘር ምንጭ...............................37**

**ኦሮሞና አማራ በዘር አወራረድ...............................................51**

## ክፍል ሦስት

በኢትዮጵያ ሥርወ-መንግሥታት ውስጥ የአማራው ተሳትፎ መጠን.................................................142

የዘመነ መሳፍንት ክስተት...................................................198

የንግሥተ-ሳባ ማንነትና ስለ መኖር አለመኖርዋ......203

ማጠቃለያ እና መደምደሚያ------------------------.-256

**ዋቢ መጻሕፍት**...................................266




የኦሮሞ እና የአማራ እውነተኛው የዘር ሐረግ ምንጭ ፍቅሬ ቶሎሳ

# ስለደራሲው አጭር መረጃ



ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ ጂግሳ፣ /ፒ.ኤች.ዲ./ ገጣሚ፣ ጸሐፌ-ተውኔት እና ከ60 በላይ መጽሐፎችንና መጣጥፎችን በአማርኛ፣ በጀርመንኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች አሳትሞ ለንባብ ያበቃ ምሁር ነው። The Hidden and Untold History of *The Jewish People*

*and Ethiopians* የሚለው የወሪጅናሌ ታሪክ እና Heaven ገ Eden የተሰኘው ተውኔታዊ የፍልስፍና መጻህፍቱ የቅርብ ጊ ሥራዎቹ ናቸው። በጀርመን እና በአሜሪካ በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎ ውስጥ አስተምሯል። በተጨማሪም የተወሰኑ የተውኔት ሥራዎቹ በአሜሪካ እና በኢትዮጵያ ለመድረክ አብቅቷል። ኢትዮጵያ ውስ በመድረክ ከቀረቡት ተውኔቶቹ መሃል ‹‹ጓደኛሞቹ›› (መቃብ ቆፋሪውና የሬሳ ሳጥን ሻጩ)፣ ‹‹ፍቅር ባሜሪካ› እና ‹‹ስንዝር መሬት ይገኙበታል። "ባለ ብዙ ቀለማት አበባ-Multi-Colored Flowe በሚል ርዕስ ያዘጋጀው ፊልም በአሜሪካ፣ በካናዳ፣ በአውሮጳ አ በኢትዮጵያ ታይቶ ታላቅ ውይይት ቀስቅሷል። የተወሰኑ ግጥሞ በጀርመንኛ በመጻሕፍት ታትመው ለንባብ ቀርበዋል። የኖቤል ሎሬቶ ለምሳሌ Gabriel Garcia Marquez, Adolfo Perez Esquivel አ Javier Perez de Cuellar, የቀድሞው የተባበሩት መንግሥታት ዋ ፀሐፊ ሥራዎች ጭምር በታተሙባቸው በዓለም-አቀፍ ገጣሚያን እ ደራሲያን ምርጥ ሥራዎች መድብሎች ውስጥም ስራዎ ተካትተዋል።

የፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ ጂግሳን ግጥሞች የሚወድ አንድ የታዋ የጀርመን ሙዚቃ ደራሲ ግጥሞቹን ከሙዚቃ ጋር በማቀናበ ለጀርመን ሙዚቃ አድማጮች አቅርቦአቸው አድናቆቱንና አክብሮቱ ገልጾለታል። *Promise Fulfilled* የተሰኙ ተውኔታዊ ግጥመ በመታተም ላይ ነው። "Encyclopedia of African Literature' በተሰኘው መጽሐፍ ውስጥ "Who is Who in Poetry" በሚለው የአሜሪካ ታዋቂ ገጣምያን መድበል ላይም ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ ጂግሳ የክብር ቦታውን ይዟል። ባሁኑ ወቅት አሜሪካ ውስጥ በኦክላንድ፣ ካሊፎርንያ በሊንከን ዩኒቨርሲቲ የሁማኒቲስ ፕሮፌሰር ነው።





# መቅድም

በተለይ የኦሮሞን ምንጭ፣ ባጠቃላይ ደግሞ ኦሮሞ ከአማራ ጋር ያለውን ዝምድና በተመለከተ አጅግ ግራ መጋባት አለ። ኦሮሞዎች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ማለትም የዛሬ 500 ዓመት አካባቢ ከእስያ ተነስተው በማደጋስካር አቋርጠው ወደ ኢትዮጵያ የመጡ የውጪ ወራሪዎች ተደርገው እጉል ስም ይሰጣቸዋል። ኦሮሞው መጤ ነው ወይንስ ሃገር-በቀል?

ስለ አማራ ማንነትም ቢሆን ሁሉም የታሪክ ሊቃውንት ርግጠኞች አይደሉም። ከኦሮሞ ቀድመው ከደቡብ አረቢያ የፈለሱ ናቸው የሚሉ አሉ። አማሮች አንደ ሴማዊ፣ ይባስ ብሎ ደግሞ እንደ ሃበሻ ይታያሉ። አማሮች በእውኑ እነዚህን ናቸውን? አማሮች ነገሥነገሥታት እና ንግሥተነገሥታት ሆነው ሳለፉት 3000 ዓመታት እንደገዙት አንደሰለሞን ሥርወ-መንግሥት አባላት ተቆጥረዋል። አማሮች ይህን ሁሉ ነበሩን? የኦሮሞዎችና የአማሮች እውነተኛው ምንጭ ከየት ነው? ይህ መፅሐፍ በነዚህ መደናገሮች እና ጥርጣሬዎች ላይ ብርሃን ፈንጥቆ እውነቱን ያጠራል።

አማራው በሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥት ውስጥ ዋናው የሥልጣን ባለቤት እንደነበረ ተቆጥሮ እስከዛሬ ድረስ ለዘር ጥቃት ሲጋለጥ፣ ሲፈናቀል ሲሰቃይ እና ሲገደል ኖሮአል። ምንም አንኳ ከነበረው ከማንኛውም ክመንግሥት አና የወታደራዊ ሥልጣን ከተገለለ 40 ዓመታት ያለፉ ቢሆንም አሁንም ሥልጣን ላይ እንደ አለ እየተቆጠረ የዘር ጥቃት ሰለባ ሆኖ ይገኛል። በርግጥ አንዳንድ የጎሳ እና የፖለቲካ ቡድኖች አርስ በርሰቸው ሙሉ በሙሉ ተፃራሪዎች ሆነው ሳለ ህብረትና አንድነት ለመፍጠርና ሥልጣን የመያዝ ፍላጎታቸውን ለማሳካት አማራውን እንደ ጋራ ጠላታቸው ቆጥረው ፀረ-አማራነትን የመሰባሰቢያና የመጠናከሪያ ብልሃት አድርገው ሠርተውበታል። አማራውን የጋራ ጠላታቸው አድርገው ባይተባበሩ፣ ባይዋሃዱና አንድነት ባይፈጥሩ ኖሮ የትግላቸው ውጤት ፍጹም የተለየ በሆነ ነበር። አውን አማራው ሳለፉት 3000 ዓመታት ዋናው የኢትዮጵያ ገዢ ሃይል ሆኖ ኖሯልን? አማሮች የአማራ ስርወ-

መንግሥት የሚል መስርተው ኢትዮጵያን የገዙበት አጋጣሚስ አለ? አማራውን እወክላለሁ ብሎ ያወጀ ንጉሠ-ነገሥትስ ይኖር ይሆን? ስመሆኑ በአለፉት 700 ዐመታት ኢትዮጵያን የገዛ ኦሮሞው ነው ወይንስ አማራው? እንደዌው ለነገሩ በኢትዮጵያ ሥርወ-መንግሥታት ውስጥ የአማሮች ተሳትፎ ምን ያህል እና እስከ ምን ድረስስ ነበር? እስከነአካቴው አማራ የሚባል ህዝብ አለ ወይስ የለም? ንግሥተ-ሳባስ ተረት ነች ወይንስ እውን? ፊደላትን በተመለከተ ለኦሮሞዎች የሚበጀው በላቲን ወይንስ በኢትዮጵያ ፊደላት መጻፍ? እነዚህን ሁሉ ዐቢይ ጉዳይዎች መመርመር የዚህ መፅሃፍ ዋና ዓላማ ነው።

ይህ ፅሑፍ ህተታ እስካሁን የነበሩና የተለመዱ አንዳንድ መሰረታዊ ግንዛቤዎችን ሙሉ በሙሉ ውድቅ የሚያደርግ አዲስ ታሪክ ነው። ታሪኩ የተመሠረተውም በመጽሐፍ መደብሮች በሚገኙ የአማርኛ እና የእንግሊዝኛ ሥነ-ጽሑፎች ላይ ነው። ከእነዚህ ጽሑፎች ውስጥ ሱዳን ኑቢያ፣ ጀበል ኑባ በተባለ ስፍራ በአንድ የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ፍርስራሽ አጠገብ ተቀብረው መሬራስ አማን በላይ በተባለ ወጣት መናኝ ከ50 ዓመት በፊት የተገኙና አጥረውና ወደ አማርኛ ተተርጉመው "መጽሐፈ ሱባኤ" እና "የኢትዮጵያ ትንሣኤ ታሪክ" በሚሉ ርዕሶች የታተሙ ጥንታውያን የግዕዝ ብራና ጥቅሎች ይገኙባቸዋል። እነዚህ የኢትዮጵያ ብራና ጥቅሎች እሥራኤል አገር ኩምራን በተባለ ዐታ በአንድ ዋሻ ውስጥ በአረኞች ከተገኙት የሙት ባሕር ብራና ጥቅሎች ጋር ተመሳሳይነት አላቸው። እነሱ፣ እነዚህና ሌሎችም መጽሐፎች ከስድስት ዓመት በፊት ድንገት እጄ ገቡ። መጽሐፎቹ በስፋት ለሕዝብ የቀረቡ እና በሐገር ውስጥም ሆነ በውጪ ሐገር ለበርካታ ሰዎች ደርሰው የተነበቡ ናቸው። ከመጽሐፎቹ መገኘት ጋር በተያያዘ ስማቸው መጠቀስ ያለበትና ለኛ ለኢትዮጵያውያን ባለውለተኞች የሆኑ ሁለት የባህላዊ ታሪክ አዋቂ ኢትዮጵያውያን አሉ፤ እነሱም አክሱማዊው ሲራክ እና የቤተ-እንዳው ዘግዱር (ዘግዱር ዘቤተ አንዳ) ናቸው።

አክሱማዊው ሲራክ በአክሱም የንጉሠ-ነገሥት ውድም አስፈሪ ልጅ ከነበረው ከሕዝበ ባርኮ የሚወለድ ልዑል ሲሆን የቤተ-መንግሥቱ መፃህፍት ያዥ እና ንብረት ሃላፊም ነበር። እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ879 ዓ.ም አስቴር በመባል የምትጠቀሰው ዮዲት ጉዲት በወቅቱ የነበረውን መንግሥት ገልብጣ መኳንንቱን ልትገድል ስታሳድድ





አክሱማዊው ሲራክ መጽሐፈ ሱባኤን እና ሌሎችንም ጠቃሚ ቅርሶችን ይዞ ከአክሱም ወደ ግብፅ ተሰደደና በኑቢያ ተቀመጠ። በመጽሐፈ ሱባኤ ውስጥ ታሪከ-ነገሥት ዘኢትዮጵያ የተሰኘ ሌላ መጽሐፍም ነበር። ታሪከ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ከቀዳማዊ ኢትዮጵ ጀምሮ በዮዲት እስከተገለበጠው የመጨረሻው የአክሱም ንጉሠ-ነገሥት እስከ ንጉሥ ውድም አስፈሪ ድረስ የነበሩትን ነገሥታት የሚዘረዝር ነው። አክሱማዊ ሲራክ ታሪከ ነሥትን ጨምሮ መጽሐፈ ሱባኤን ከግእዝ በፊት ከነበረው ከጥንቱ የሱባ ቋንቋ በሦስት ቋንቋዎች ተርጉሞ ለትውልድ እንዲደርስ አድርጓል።

ቀደም ሲል ግብፅ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ አማራ ወታደሮችን ከ 290 ዐመታት በሁዋላ ላሊበላ አሰባስቦ በኑቢያ በኩል ሲያልፍ የኑቢያ ንጉሥ ምንአልባት የአክሱማዊ ሲራክን መጽሐፈ ሱባኤ ቅጂ ሰጥቶት ይሆናል። አፄ ላሊበላም መጽሐፎቹን በደስታ ወደ ኢትዮጵያ አምጥቶና በቅጅዎች አባዝቶ በቤተ-መጻሕፍቱ አኑሯል። በኋላ ደግሞ በ15ኛው ክፍለ-ዘመን ታላቁ ንጉሠ-ነገሥት አምደ ጽዮን ቅጂዎችን አባዝቶ በተለያዩ ገዳማት አኖራቸው። ይህን ያደረገው አንድም የጠፋውን የኢትዮጵያን ታሪክ ለማዳን ወይም መጽሐፉ የግብፅን ታሪክ የሚያስከነዳውን የኢትዮጵያን እውነተኛ ክብረ-ዝና ስለሚያንፀባርቅ እና የግብፅ ፓትሪያርክ በዚህ ስለሚቀና መጽሐፉን ለማጥፋት ከሚያስማራቸው ተከታዮቹ ለመጠበቅ ሲል ነበር። ነገርግን ክፉ እድል ሆነና ፓትሪያርኩ በሚተባበሩት ቀሳውስት አማካኝነት ከአምደጽዮን ጀርባ በምስጢር ያስተላለፈው ትዕዛዝ ተግባራዊ ሆኖ በርካታ የመጽሐፉ ግልባጮች ሲወድሙ በአጋጣሚ ዘግዱር ዘአንዳቤት ወይም የቤተ አንዳው ዘግዱር በተባለ ጸሓፊና የታሪክ አዋቂ እጅ የነበረ አንድ ቅጅ ብቻ ተረፈ።

ዘአንዳቤት ወይም ቤተ አንዳ መጽሐፍት በእጅ የሚቀዱበት ዐታ ሲሆን በዚያን ጊዜ በእጅ የሚገለበጠው መጽሐፍ ጥራቱ በማተሚያ ቤት የሚታተመውን ያስንቅ ነበር። የሚገርመው ነገር ምናልባት ያም ሰው በ17ኛው ክፍለ-ዘመን በአዲያም ሰገድ ኢያሱ ዘመነ መንግሥት ያንኑ አንድ ቅጂ ይዞ ወደ ተለመደው አገር ወደ ኑቢያ ተሰዶ ይሆናል። አለዚያም መፅሀፉ በሌላ ሰው ወደዛ ተወስዶ ለኛ ለተተኪዎቹ ትውልዶች ይደርስ ዘንድ ከአንድ የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርትያን ፍርስራሽ ጎን ከሚገኝ ከትልቅ ቁዋጥኝ ከተፈለፈለ አለት

ውስጥ ተቀምጦ ሳለ ቤተ ክርስቲያኑ በአረብ ሙስሊሞች ሲቃጠል መጽሐፉ አለቁ ውስጥ ተረፈ። ያንን መጽሐፍ ነው መሪራስ አማን በላይ አግኝቶ ወደ ኢትዮጵያ ያመጣው። የብራና ጥቅሎቹ የተፃፉት በግዕዝ ነበር። ወደ ኢትዮጵያ ያመጣልንና የእውነተኛው ታሪካችን ብርሃን እንደገና እንዲበራ ያደረገልን መሪራስ አማን በላይም ባለውለታችን ነው። በመሆኑም ምስጋና ይገባዋል።።

መሪራስ አማን በላይ በመጽሐፈ ሱባኤ ውስጥ ተካትተው ካገኛቸው መጻሕፍት ውስጥ በትልቁ ነብይ በሄኖክ የተጻፈውና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ "የሠራዊት ጌታ ጦርነቶች መጽሐፍ" በሚል የተጠቀሰው ስለ ዓለም አፈጣጠር የሚተርከው "መጽሐፈ ጃን ሸዋ" ይገኝበታል። ሙሴ ከአማቱ ከጀትሮ (ዮቶር-አብ) ጋር በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በነበረበት ወቅት በኛ እጅ የነበረውን ይህን መጽሐፍ አግኝቶ ነው "ኦሪት ዘ ፍጥረት" የተሰኘ መጽሐፉን ከኛው መፅሐፍ ላይ ቀንጭቦ የጻፈው።

አማን በላይ እንደሚለው የተገኙት እና ለኛ የደረሱት የብራና ጥቅሎች የመጀመሪያ ጽሑፎች ሳይሆኑ የብራና ላይ የእጅ ቅጂዎች ናቸው። በዚያን ዘመን ማተሚያ ቤት አልነበረም። ስለዚህ የቁም ጸሐፊዎች ለራሳቸው ወይም ለደንበኞቻቸው መጽሐፎችን አሳምረው በእጅ ይገለብጡ ነበር። እነዚያ የብራና ጽሑፎች ከ350 ዓመታት በፊት ኢትዮጵያን ይገዛ የነበረው ንጉሥ ማን እንደነበር ለሙን ይጠቅሳሉ። አሉም አዲያም ሰገድ ኢያሱ ነበር። መፅሐፎቹ ከዚያ በኋላ ስለማንም የኢትዮጵያ ንጉሥ ወይም ድርጊት የመዘገቡት ነገር የለም። ይህም በመሆኑ ምንም እንኳን የሚተርኳቸው ታሪኮች ጥንታውያን፥ ማለትም ከ 4000 ዐመታት በላይ ቢሆኑም፥ ጥቅሎቹ ቢያንስ 3500 ዓመት እድሜ እንዳላቸው እንገምታለን።

እንግዲህ በነዚህ ምክንያቶች ነበር የዝነኛውን ታሪካችንን ጎዳና የሳትነው። በመሆኑም ኦሮሞዎች ከእስያ፣ አማሮች ደግሞ ከአረቢያ እንደመጡ አሰብን። ለዚያ ነበር አማሮችን እንደ ሴማዊ፣ ኦሮሞዎችን ደግሞ እንደ ኩሻዊ የቆጠርነው። ሀቁ ግን ሁለቱም ኩሻውያን እንደነበሩ እና ከአንድ አባት ደሴት ወይም ደሽት ከተባለ መፍለቃቸው፤ ከአንድ አካባቢ ከጐጃም፤ ከአንዲት አገር ከኢትዮጵያ መገኘታቸው ነው። ምንጫቸው በተለይም ፈላስፋ እና ካህን እንዲሁም





የኢትዮጵያ መስራች የነበረው የኢትዮጵ ዝርያ ከሆነው በዚሁ በደሼት ወይም ደሴት ሥም እስከ ዛሬ ከሚጠራው ከጣና ሃይቅ አካባቢ ከኖረው ከደሽት ነው።

በእነዚህ መጽሐፎች አዲስ ከተካተቱት ጠቃሚ መረጃዎች ውስጥ ቀዳማዊ ኢትዮጵ ኢትዮጵያ ለምትባለዋ አገር መሥራች የሆነው ንጉሠ-ነገሥት ለኦሮሞ፣ ለአማራ እና ለሌሎችም ኢትዮጵያውያን ሁሉ ቀደምት አባት መሆኑ መገለጹ ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ ለእኛ ለዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያን መገኛ የሆኑትን የኢትዮጵን ልጆች እና የልጅ ልጆች ስም ዝርዝር የያዘው የዘር ሐረግ ሰነድም ይገኝበታል። የጥንት የኦሮሞና አማራ ምሁራን፣ ፈላስፎች፣ ነቢያት እና ካህናት ታሪካቸውንና እውቀታቸውን ለመፃፍ የተጠቀሙበትን የሱባን ፊደልም ፈጥረው እንደ አስተላለፉልንም ይዘግባል።

እነዚህን መጽሐፎች ካገኘሁ በሁዋላ ነበር በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ የነበረኝ የግንዛቤ አቅጣጫ ሙሉ ለሙሉ የተቀየረው። ይህም ከ25 ዓመት በፊት ስለ ኦሮሞ ሥረ-መሠረት እና ስለ አማራና ትግሬ ታሪክ በአውሮፓውያን "የኢትዮጵያ ታሪክ ጥናት ጠበብት" ተብዬዎች በደረደሩልን የጠነዙ ገለፃዎች ላይ ተመስርቼ አዘጋጅቻቸው የነበሩትን ጽሑፎች እንድከልስ አድርጎኛል።

ታሪካችን በጊዜ ክፍተት ውስጥ ሲያልፍ በተቃራኒ ሃሳቦች የመቀየጥ እና የመድበስበስ አደጋ አጋጥሞታል። አሁን ግን ሀቁ ፍንጥጥ ብሎ ወጥቷል። እውነት ተቀብራ አትቀርም። እነዚህ አዳዲስ መረጃዎች በመቶዎች ለሚቆጠሩ ዓመታት ኢትዮጵያን ስለገዙ ኦሮሞ ንጉሦችና ንግሥቶች እንዲሁም ሁለቱም ኦሮሞና አማራ ለኢትዮጵያ ስልጣኔ ስላበረከቱት አስተዋጽኦ ቀደም ሲል የፃፍኳቸውን ጽሁፎች የሚያጠናክሩ ሆነዋል። በርግጥ ጽሁፎቹ በነዚህ ርዕሶች ላይ ቀድሞም ምሉዕ ነበሩ። አዲሶቹ ግኝቶች የጽሁፎቼን ትክክለኛነት የማረጋገጥ ሚና ነው የተጫወቱት። እንዲሁ እነዚያን ጽሁፎቼንና በዚህ መጽሐፍ መጀመሪያ ላይ ያስቀመጥኩትን "ለኢትዮጵያ ስልጣኔ የኦሮሞ አስተዋጽኦ" የሚለውን ጨምሮ በኢትዮጵያን ሪቪው እና በኤሌክትሮኒክ ሚዲያው ላይ ወጥተው የነበሩ ጥቂት መጣጥፎችን ከመጠነኛ ማሻሻያ ጋር በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አካትቻለሁ።

ከነዚህ መጣጥፎች ውስጥ አንዳንዶቹ ስታዋቂ መጽሔቶች የተፃፉ ስለነበሩ በጥቅሶች እና ማጣቀሻዎች የተጠናከሩ አልነበሩም። ምንጭ የተጠቀስሳቸው አንገብጋቢ በሆነበት ቦታ ላይ ብቻ ነበር። በኦሮሞና በአማራ አመጣጥ ታሪክ ላይ የቀረበው ይህ ሥራ ግን በበርካታ ጠንካራ ማስረጃዎች የተደገፈ እንዲሆን ተደርጓል።

ፈረንጆቹ የጻፉልን ታሪካችን ወጣቶቻችንን በማንነት ቀውስ የከተተ ከመሆኑም በተጨማሪ እርስ በርሳችን አንዳንግባባ እና እንዳንተማመን ከማድረግም አልፎ ደም ያፋሰስም ሆኗል። ከሁሉም በላይ ደግሞ እያንዳንዱ ብሔረሰብ ለኢትዮጵያ ሕልውና እና ስልጣኔ ያደረገውን አስተዋጽኦ እና ክብር እንዳናውቅ ብሎም እንዳናደንቅ እንቅፋት ሆኖብን ቆይቷል። ይህ *"የኦሮሞና የአማራ እውነተኛው የዘር ምንጭ"* የተሰኘው መጽሐፍ ግን በኛ በኢትዮጵያ ልጆች መካከል ያለውን ያለፈ ጥርጣሬ አጽድቶ፤ መነሻ ምንጫችንን አሳይቶ፤ በአኩሪ የጋራ ታሪካችን ውስጥ ሁላችንንም አካትቶ፤ ወደ ሰላም እና ስምምነት እንድንመጣ መርቶ በመካከላችን እውነተኛ የወንድማማችነት መንፈስ ያስፍናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

እውነተኛ ታሪካችን እስከሚመሰክረው ድረስ ሁላችንም ኢትዮጵያውያን የኢትዮጵ ልጆች የሆንን ወንድማማቾች እና እህትማማቾች ነን። ሆኖም ይህ ጽሑፍ በኦሮሞ እና በአማራ ላይ ብቻ ነው የሚያተኩረው። በመሆኑም ተልእኮው ውሱን ነው። ለወደፊቱ የሌሎቹም ኢትዮጵያውያን እውነተኛ ታሪክና ዝምድናም በጥልቀት ተጠንቶና ተጽፎ እንዲቀርብ ምኞቴ ነው።

የዳግማዊ አፄ ምኒልክን፣ የይኩኖ አምላክን፣ የኢትዮጵንና የተወሳጆቹን፣ ለምሳሌ የአፄ እስያኤል ወይም እሴ እንዳንዴም አፄ የሚባለውን ታላቅ ንጉሠነገሥት ታሪኮች ሆን ብዬ ምንም ለውጥ ሳላደርግባቸው ካንድ ጊዜ በላይ በዚህ መጽሐፍ መነሻና መድረሻ ላይ እንዲቀርቡ አድርጌአለሁ። የተወሰኑ ታሪኮችም ይደጋገማሉ። ይህ የሆነው አንድም መጽሃፉን የደረስኩት በተለያዩ ጊዜያት በመሆኑ፣ አንድም የአንባቢውን አዕምሮ ለማደስ እና ታሪኮቹን ወደ ልበ-ልቦናው ለማድረስ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ድግግሞሽ የመጽሐፉ ጠባይ እና ግዴታም ስለሆነ ነው። አንባቢዬ ድግግሞሹን ካልፈለገ ችላ ብሎ ይዝለለው።





በኢትዮጵያችን ውስጥ ሁለት አክራሪ ወገኖች ይስተዋላሉ። ባንድ ወገን ኦሮሞን ጨቁኖ ሲገዛ የኖረው አማራው ነው የሚሉ የተወሰኑ ሰዎች አሉ። እነዚህ ጥቂት ኦሮሞዎች ከአማራው ጋር፤ የኢትዮጵያ መስራች ከሆነው ከኢትዮጵ ጋር፤ ከራስዋ ከኢትዮጵያ ጋር፤ ከሰንደቅ ዓላማዋም ጋር ምንም የሚያገናኘን ነገር የለም ይላሉ። በተጨማሪም አማራው የኦሮሞን ሰም መሬት ይዟል ብለው ስሚያስቡ ከኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ኦሮምያ የተሰኘች ክልል ነጥለን እናወጣለን ባዮች ናቸው። እንዲሁም በአማራው ጎሣ፤ በአማራው ባሕል እና በቋንቋው ባማርኛ ላይ ጥላቻ አላቸው። የአማራውን ባሕል እና ቋንቋ የሚጠሉት በግድ ተጭኖብናል ብለው ስለሚያስቡ ነው። ከዚህ አልፈው ተርፈው ቋንቋችንና ባህላችን በአማራው ተደምስሶአል ይላሉ። ይህ አባባል እውነት መሆን አለመሆኑን ይህ ፅሁፍ በማስረጃ ላይ ተደግፎ ያረጋግጣል።

በሌላ ወገን ደግሞ በ16ኛው ክፍለ-ዘመን የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት አጼ ልብነ-ድንግልና ወራሻቸው በግራኝ ወረራ በተወጠሩበትና አማሮች ንጉሠ-ነገሥታቸውንና አገራቸውን ለማዳን በሚፋለሙበት ወቅት ኦሮሞዎች አጋጣሚውን ተጠቅመው ከእስያ በማደጋስካር በኩል መጥተው የአማራን መሬት የያዙ ወራሪዎች ናቸው የሚሉ የአማራ ጽንፈኞች አሉ። በዚህ ምክንያት እነዚህ አክራሪ አማሮች ለኦሮሞዎች ለባሕላቸውና ለቋንቋቸው ዝቅ ያለ አመለካከት አላቸው። ከሁሉም በላይ ደግሞ እነዚህ ጥቂት ተስፈንጣሪዎች ራሳቸውን እንደ ገዢ መደብ አባላት ቆጥረውም ይኩራራሉ።

እነዚህ ሁለት ተፃራሪ ወገኖች በጎጂ አመለካከቶቻቸው አብሮ በሰላም፤በጋብቻ እና በፍቅር ለዘመናት ሲኖር የነበረውን የብዙሓኑን ኦሮሞና አማራ ሕይወት ለአደጋ አጋልጠዋል። ለሰላም፤ ለእኩልነት፤ ለመቻቻል እና ለአብሮ መኖር እንቅፋት ሆነዋል። ልቦና ካልገዙ ሁለቱን ህዝቦች ሳላስፈላጊ ብጥብጥ እና ደም መፋሰስ መዳረጋቸው አይቀርም። ጠንቁ ደግሞ ለሌሎቹም ኢትዮጵያውያን ይተርፋል። ሁለቱ ኃያላን ህዝቦች እየተጣሉ ሌሎቹ በገለልተኛነት በሰላም ይኖራሉ ማለት ዘበት ነው። ስለዚህ መፍትሔ መፈለግ አለበት። መፍትሔው በነዚህ በሁለቱ ተፃራሪ ሃይሎች እና አመለካከቶች መካከል አማካይ መንገድ መሻት ነው። ይህ ጽሑፍ አድሎአዊ ባልሆነ ጠንካራ ማስረጃ ላይ የተመሰረተ፤ ክፍተቱን በማጥበብና በሁለቱ ኃይሳት መካከል አንደ

ድልድይ ሆኖ በማገልገል በሁለቱ ሕዝቦች እና ባጠቃላይም በኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል ስምምነት፣ መግባባት፣ ፍቅር፣ እኩልነት፣ የርስበርስ መከባበር፣ መቻቻል እና በሰላም አብሮ የመኖር ባሕል ያመጣል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ ጂግሳ

ቫሌሆ፣ ካሊፎርኒያ

እ.ኤ.አ መጋቢት 24 ቀን 2016 ዐመተ ምህረት





# ክፍል ዐንድ

## ኦሮሞ ለኢትዮጵያ ስልጣኔ ያበረከተው አስተዋጽኦ

ፕሮፌሰር ኤ. ኡሉንዶርፍ ኢትዮጵያውያኖቹ *‹‹The Ethiopians››* በተሰኘው ዝነኛ አጭር ጽሑፋቸው ውስጥ ***‹‹ኦሮሞዎች ለኢትዮጵያ ስልጣኔ ያበረከቱት አስተዋጽኦ የለም››*** ሲሉ ጽፈዋል። አያይዘውም ***“ትርጉም ያለው ቁሳዊና አዕምሯዊ ባሕል የላቸውም”*** ብለዋል።(1)

እንዲህ ዓይነቱ መሰረተቢስ አባባል ብዙውን ጊዜ የሚሰነዘረው ተነገነበታል በሚሉት ዘርፈ-እውቀት ላይ ግልብ መረዳት ባላቸው *“የኢትዮጵያ ጥናት ሊቃውንት”* ተብዬዎች ነው። እንደዚህ ያሉትን የውጪ ሰዎች እምነው በመቀበል ነው እንግዲህ የኛ ምሁራን ስለ ሀገራቸው እና ስለ ሕዝባቸው የተሳሳተ ግንዛቤ የቀረፁት። ስለዚህ አገራችንን ለማጥናት እና የሕዝባችንን ትክክለኛ ማንነት ለመገንዘብ እኛው ራሳችን፣ በራሳችን፣ የራሳችንን ጥናት ማካሄድ አለብን። ፕሮፌሰር ኡሉንዶርፍን እንዲህ ዓይነት የተሳሳተ መደምደሚያ ላይ ለመድረስ ያበቃቸው ምን እንደሆነ አላውቅም። ምናልባት ኦሮሞ ሥነ-ጽሑፍ የለውም ከሚል ስህተት ተነስተው ከሆነ እዚህ መደምደሚያ ላይ የደረሱ ግምታቸው ፍፁም ሚዛን አይደፋም።

በደምሳሳው አነጋገር አንድ ሕዝብ የጽሑፍ ሥነ-ጽሑፍ ባያኖረውም እንኳ ቁሳዊ እና አዕምሮአዊ ባሕል ይጐድለዋል ማለት አይደለም። የሰፊው ሕዝብ አዕምሮአዊ ባሕል በጥልቀት ሰርጾ የሚገኘው በስነ-ቃላቸው ውስጥ ነው እንጂ በስነጽሑፍ ውስጥ አይደለም። የባሕላዊ ሀብት ግዙፍ የደም ስር የሚገኘው በስነ-ቃል እና በሥነ-ምግባር እሴቶቻቸው፣ በማኅበራዊ ተቋሞቻቸው እና በትውፊቶቻቸው ውስጥ ነው። ስነ-ቃል ብቻ የብልኀነታቸውን፣ የቤተሰቦቻቸውንና የቡድን ግንኙነቶቻቸውን ጥልቀት እና ባሕሪያቸውን ሲያንፀባርቅ ይገኛል። እንደ ሁሉም የዓለም ሕዝቦች ሁሉ የኦሮሞ

ቤተሰብ ጥበቡን፣ ብልኃቱን እና ፍልስፍናውን በምሳሌው፣ በአባባሉ፣ በባሕላዊ ዘፈኑ እና በአውደ-ተረቱ፤ ባጠቃላይ በሥነ-ቃሉ ውስጥ ይገልጻል። ፕሮፌሰር ኡሉንዶርፍ የኦሮሞን ስኬት ለመለካት የሞከሩበት መለኪያ ምንም ሆነ ምን ለባሕላችን ፍትሀዊ እና ግንዛቤአዊ ጥንቃቄ የነበረው አይመስለኝም። ለ3500 ዓመታት በመካከላቸው በነበረው የሥጋ ዝምድና፣ የጋብቻ እና የባሕል መስተጋብር የተነሳ የኦሮሞ ሕዝብ ለአማራ ባሕል ያበረከተውን አስተዋጽኦ ቀጥሎ ባጭሩ እነድፋለሁ።

አማራዎች በሕዝብ ብዛት ከኦሮሞ ቀጥሎ ከፍተኛውን ቁጥር ይይዛሉ። በዚህ የተነሳም በኢትዮጵያ የነፃነት ታሪክ በውትድርና፣ በትምህርት፣ በክህነት፣ በፖለቲካ እና በባሕል የነበራቸው ሚና ላቅ ያለ ነበር። በመሆኑም ኦሮሞዎች ለአማራ ስልጣኔ ያበረከቱት ማናቸውም ነገር ለኢትዮጵያ ስልጣኔም የተበረከተ ነው። ሁለቱ ሕዝቦች አንድ ዓይነት የዘር ሐረግ፣ አንድ ዓይነት ታሪክ እና አንድ ዓይነት አጣ ፈንታ ስለሚጋሩ አንድ ላይ ተቀላቅለዋል። አዕምሮአቸውን ክፈት አድርገው የሥጋ ዝምድና እንዳላቸው በደንብ በመገንዘባቸው አማሮች ባለፉት ጊዜያት የኦሮሞን ባሕል እና የአኗኗር መንገዶች ተጋርተዋል። አማራዎች አብሪተኞች ቢሆኑና አንዳንዶች እንደሚመኙት ኦሮሞዎችን ቢንቁ ኖሮ የኦሮሞን ባሕልና ልማድ ተቀብለው እየተጋቡ ራሳቸውን አያዋሕዱም ነበር። ኦሮሞዎች ባሕላቸውንና ልምዳቸውን በአማሮች ላይ በግድ አልጫኑባቸውም። አማሮች ናቸው ወደውና ፈቅደው የተቀበሉት። መሳፍንቱን ገሽሽ አናደርጋቸውና ተራው የኦሮሞና አማራ ሕዝበ-ኢትዮጵያ በደምና በሥጋ ብቻ ሳይሆን ላለፉት 3500 ዓመታት በባሕል፣ በኀሊና እና በመንፈስም ተዳቅሏል፣ ተቀላቅሏል፣ ተዋሕዷል።

የኦሮሞ ሕዝብ አስተዋጽኦ በተለይ ለአማራ ስልጣኔ ባጠቃላይ ደግሞ ለኢትዮጵያ በምን መልክ እንደሆነ በመጠኑ ለማንሳት ሥነ-ልሳናዊ፣ ፍልስፍናዊ፣ መንፈሳዊ፣ ውትድርናዊ እና ቢያምኑም ባያምኑም ቅኔያዊም ነው። ክህነታዊ ጥናቶችን፣ ዳንኪራን፣ ሙዚቃንና ዕደ-ጥበብንም ይጨምራል።





## ሥነ-ልሳናዊ አስተዋጽኦ

አንዳድ ሰዎች እንደሚመስላቸው የአማርኛ ቋንቋ አበልፃጊ ግዕዝ ብቻ አይደለም። ዛሬ አማርኛ የሚመስሉን በርካታ ቃላት፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ አባባሎች እና ተረታ-ተረቶች ምንጫቸው ኦሮምኛ ነው። (ትክክለኛው አባባል ‹‹አፋን ኦሮሞ›› ነው።) አማርኛ ቋንቋ በቅርበት ሲጠና በአስተሳሰብ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ በርካታ የኦሮምኛ ቃላት፣ ምሳሌያዎችና ተረቶች በውስጡ አሉት። የአማርኛ ሰዋሰው እንኳ ከሴማዊነቱ ይልቅ ኩሻዊነቱ ያመዝናል። አንዳንድ የአማርኛ ቃላት በኦሮምኛ የምዕላድ ሕግጋት ስር ያልፋሉ። አሁን የአማርኛ መዝገበ ቃላት አካል የሆኑ የኦሮምኛ ቃላት ቁጥር የላቸውም። ቢሆኑም ጥቂቶቹን እንደሚከተለው ለይቼ አቀርባለሁ።

ኦሮሞ ያልሆኑ ሰዎች ስንቶች ናቸው ‹‹ዱላ›› የሚለው ቃል የኦሮሞ መሆኑን የሚያውቁ? በመገኛው ቋንቋው “ጦርነት” ማለት ነው ፍቺው። በአማርኛ ቋንቋ ግን “በትር” ሆኗል። ቢሆንም ፀብን ያጠቁማል። "ተራ" የሚል ፍቺ ያለው “ወረፋ” የሚለው ቃል ኦሮምኛ መሆኑንስ ስንቶች ይገነዘባሉ? ኮርማ፣ የሚሉትንስ? ጥቂት የኦሮምኛ ቃላትን ለአብነት ቀጥሎ ላቅርብ እስቲ፡-

"ሮሚማ" ሰብ ሥጋ

"ጭኮ" በለጋ ንጥር ቅቤ የተለወሰ በሶ (የገብስ ዱቄት)፣

"ሶኬካ" ደን፣

"ጉርዳላ" በራስ ላይ ሻሽ በቀጭኑ ማሰር፣

"ወጌሻ" በእጅ በማሸት ብቻ ውልቃት እና ወለምታ የሚያስተካክል፣ የተሰበረ አጥንት የሚጠግን ባህላዊ ሀኪም፤

"ደቦ" በገበሬዎች ዘንድ በዕርሻ ስራ ላይ ከጎረቤት ጋር በወንፈል ተባብሮ የመስራት ልማድ፤

"ባጂ" በዘመዳሞች መካከል ተባብሮ መስራት፤

"ጉዲፈቻ" የሌላውን ህፃን ወስዶ እንደ ራስ ልጅ ማሳደግ፤

"ደንቃራ" ከፉ አጋጣሚ እና ህመም ከራስ ተወግዶ በሌላው ላይ እንዲደርስ መንገድ ላይ በስውር የሚጣል ዶሮ፣ከብት፥ ገንዘብ ወይም ምግብ፤

"ቃልቻ" የታመመ ያድናል፣ የጠፋውን ያስገኛል፣ የተሰወረውን ያውቃል ተብሎ የሚገመት "እዋቂ፣ ባለመድኃኒት፣ ባለውቃቢ"፤

"(በ)እንጋፋ" የመጀመሪያ፣ የሁሉም ታላቅ፤

"በርጩማ" ባለ ሶስት እግር መቀመጫ፤

"ጨፌ" በለምለም ሳር የተሸፈነ ረግረግ መሬት፤

"ዳከዬ" በውሃ ላይ የምትንሳፈፍ የወፍ አይነት፤

"ጨጨብሳ" በለጋ ንጥር ቅቤ ተለውሶ እና በድቁስ በርበሬ ታሽቶ የሚበላ የተሰባበረ ቂጣ፤

"ቡራ ከረዩ" ለጠብ መጋበዝ፣ መደንፋት፤

"ገኑ" ከሃዲ፤

"ቦና" ዝናብ ያጠረው፣ ልምላሜ የራቀው የበጋ ወቅት፤

"ቦቃ" በግንባሩ ላይ ነጭ ጸጉር ያለው በሬ፣ ላም፣ ፍየል ወይም በግ፤

"ጨፌ (ጨፊ)" (ዝጋ፣ዝጊ)ዝግ ሹሩባ፤

"ወረና" ጦር፤

"ቢልቢላ" በልጆች፣ ጥጆች፣ በቅሎዎች እና ፈረሶች አንገት ላይ የሚታሰር ቃጭል፤





"አሬራ" ተንጦ ቅቤው የወጣለት ወተት፤

"አባወራ" የቤት ራስ፣ ወንዱ የቤት ባለቤት፤

"አባቢያ" የአገር መሪ፤

"አባዱላ" የጦር መሪ፤

"አባጨጓሬ" የቢራቢሮ ዕጭ እድገቱን ሲጨርስ የሚፈጠር ትል፣

"ቀልብ" ልቦና፤

"አባሰንጋ" ተላላፊ የከብት በሽታ፤

"ወዳጃ" እየተቃመ እና ቡና እየተፈላ በህብረት የሚፀለይ የሌሊት ፀሎት፤

"ባቲ" አዲስ ጨረቃ፤

"ጉባ" የከብቶች ማሰሪያ ሽቦ፤

"ቡእ/ቡቃ" የሆድ ህመም፤

"ቀዬ (የ)" ደጅ፣ ከግቢው ውጪ ያለው ባዶ መሬት፤

"አቴቴ" ሴት መንፈስ፤

"ጀብዱ" በድፍረት የተደረገ ትልቅ ድርጊት፤

"ጉማ" በገዳይ ወግን ለሟች ወገን በእርቅ የሚሰጥ የደም ካሳ፤

"ጋያ" ትንባሆ ማጨሻ

"ቱፍታ" ለምርቃት የመራቂውን ምራቅ ወይም የታኘከ ጫት በተመራቂው/በታማሚው ፊት ላይ በስሱ መትፋት፤

"ቢላዋ" የተሳለ መቁረጫ ብረት፤

“ብራ” ዝናብ ያልዘነበበት እና ጉም ያላፈነበት ብሩህ ቀን፤

“ሉሚ (ኒ”) መርዝ፣ መርዛማ ዛፍ፣ እነዚህን የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ።

ከላይ ያሉት እንግዲህ ከብዙ በጥቂቱ የጠቀስኩዋቸው ለአማርኛ ቁዋንቁዋ የኦሮምኛ የስነ-ቃላት አስተዋፅኦ ናቸው። ቀጥለን ወደ ፍልስፍናዊ አስተዋፅኦ እንሸጋገር።

## ፍልስፍናዊ አስተዋጽኦ

የኦሮሞ ሕዝብ ጥልቅ እውቀት እና ፍልስፍናዊ ንፅርዖተ-ዓለም በምሳሌያዊ አባባሎቻቸው እና በተረታ-ተርቶቻቸው ውስጥ ተንሰራፍተው ይገኛሉ። የገሃዱን ዓለም ግንዛቤያቸውንና ጥልቅ እውቀታቸውን አውጥተው የሚያሳዩ ጥቂት የኦሮሞ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ቀጥሎ አቀርባለሁ። በቅርቡ (ከ24 ዓመት በፊት) "የኢትዮጵያ እና የኬንያ ኦሮሞ ሕዝቦች ተረትና ምስሌዎች እና አባባሎች” በሚል ርዕስ በጆርጅ ኮተር ሁለት አዲስ የታተሙ መጽሐፍት ድንገት እጋጠሙኝ።(2) መጽሐፉን ስነብ በያንዳንዱ ገጽ ቢያንስ አንድ ወይም ሁለት ከአማርኛ የሚገጥሙ የኦሮምኛ አባባሎች አገኝ ነበር። በኦሮምኛ ቋንቋ ውስጥ የገቡ የአማርኛ አባባሎች ናቸው ብለው አንባቢዎች ሊወራረዱ ይችላሉ። ነገሩ እንዲህ ከሆነም መልካም ነው፤ ምክንያቱም ሁለቱ ሕዝቦች ባለፉት ዘመናት የጠበቀ ማኅበራዊ እና ባሕላዊ መስተጋብር እንዳላቸው እና እንዳቸው ሳንዳቸው እንግዳ እንዳልሆኑ ይህ ያረጋግጣል። አለበለዚያ እንድ አይነት አስተሳሰብ የሚያንፀባርቁ እንድ ዓይነት አባባሎችን እንዴት ሊጋሩ ቻሉ? እነዚህ ምሳሌያዊ አነጋገሮች አማርኛ ቢሆኑም እንኳ የተቀሩት ቁጥር የለሽ ምሳሌዎች እና ብልኅ አባባሎች ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ ትልቅ የኦሮሞ አስተዋፅኦ ናቸው።

ስማንኛውም አንድ ሰው ወይም ከላይ የጠቀስኩት ፀሐፊ እስከሚያረጋግጥልኝ ድረስ ቀጥሎ የዘረዘርኳቸውን ሁሉንም ባይሆን እንኳ አብዛኞቹን አባባሎች እንደ ኦሮምኛ ነው የምቆጥራቸው።





Dubartin keessumma hinqabdu.

የሴት እንግዳ የለውም።

Tuma keessat kilen milaan adeemti.

ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሄዳል።

Simbiron laga, laga afaan, afaan dubati.

Bakkaeetettidaaki, daakunnnaagali.

የትም ፍጪው፣ ዱቄቱን አምጪው (አስገቢልኝ)።

Hagan qaniin naabahu, garbitcha abbaa kootitin heruma jette intalli.

ቀን እስኪያልፍ ያባቴ ባሪያ ያግባኝ (አለች ልጂቱ)።

Harren funyo kutte jennan, ofiti gabaabsite jehde.

አህያ (በቅሎ) ገመድዋን በጠሰች ቢሉት፣ ለራስዋ አሳጠረች፣አለ፡

Muka jigetti qottotu bay-yata.

የወደቀ ግንድ ምስጥና ምሣር ይበዛበታል።

Abju soda irriba hindhabani..

ሕልም (ቀዠት) ፈርተው ሳይተኙ አያድሩም።

Qaallun ka nisi himbeektum kan namaa fogdi.

ጠንቋይ የራሱን አያውቅም፤ የሰው ይጠነቁላል።

Soddata ulen saa kudhan.

የፈሪ በትር ዐስር ነው።

Nama gadi jedhe nyaatu tchiisani kajeelu.

አንንብሶ የሚበላን ተኝተው ይቀላውጡታል (ይከጅሉታል)።

Haaren yo sierra kkaayan daarrarra gangalatti.

አህያ (የአህያ ሥጋ) ከአልጋ ሲሉት ከአመድ።

Na argaa na argaa kan jettu na dhossaa, na dhossaa jetti.

ዕዩኝ ዕዩኝ ያለች፣ ደብቁኝ፣ ደብቁኝ አለች።

Haaren gaafan du-e morgi hinbiqilin jettee.

አህያ፣ እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል፣ አለ።

Quufan male hinutaalan, utalani male hintchabani.

ካልጠገቡ አይዘሉ፣ ካልዘለሉ አይሰበሩ።

Raadi hare wajiin oltu, deu dhuufu barti.

ከአህያ የዋለች ጊደር ፈስ ተምራ ተገባለች።

Harren khittu ilkan wa-irra hinfithu.

አህያ ለአህያ ቢራገጥ ጥርስ አይሳበርም።

Bishan dhagaa dubbissa.

ውሀን የሚያናግረው ድንጋይ ነው።

Mana ormaa bareedaorra, godo offi wayya.

ከሰው አዳራሽ የራስ ጎጆ ይሻላል።

Nammi gabaaban utu ulfina hinqbattin dua.

አጭር ሰው አንቱ ሳይባል ይሞታል (ያረጃል)።





ከላይ ከተዘረዘሩት ምሳሌያዊ አነጋገሮች እና ብልኅ አባባሎች የኦሮሞዎችን አእምሮአዊ ኃይል እና ለአማርኛ ምሳሌያዊ አነጋገር ያበረከቱትን አስተዋጽኦ እንድንረዳ ያግዛሉ። አንዳንድ የኦሮምኛ ቃላት ለምሳሌ "ከጀሉ" እና "ሂንቢቂሉን" የሚሉትን ቃላት አንደቅደም ተከተላቸው "ከጀለ" እና "በቀለ" ከሚሉት የአማርኛ ቃላት ጋር አንድ ዘር መሆናቸውን እንገነዘባለን። ባለፉት ዘመናት ኦሮሞና አማራ ካልተቀላቀሉ በስተቀር ይህን መሳይ የቃላትና የምሳሌያዊ አነጋገሮች መመሳሰል በምን ታምር መጣ? በኦሮሞ ምሳሌያዊ አነጋገሮች እና ቃላት ላይ ይበልጥ የሚደረግ ጥልቅ ጥናት ኦሮሞንና አማራን አንድ ላይ ስላስተሳሰሯቸው የጋራ ምክንያቶች ይበልጥ መታወቅ የተሻለ መረጃ ያስገኝ ይሆናል።

## መንፈሳዊ አስተዋጽኦ

ኦሮሞው በአማራው ሃይማኖታዊ ባሕል ላይም ጉላ ያለ ተጽእኖ አሳድሯል። ኦሮሞ ዋቃ ‹‹ዋቀ›› እያለ በሚጠራው እና ሰማይንና ምድርን በፈጠረ አንድ እግዚአብሔር ያምን ነበር። አሁንም ያምናል። ዋቃ ‹‹ዋቀ›› መንፈስ ሲሆን አያና ‹‹አየኑ›› እና ‹‹አውሊያ›› በሚባሉ ትናንሽ መናፍስት የተከበበ ነው። ከነዚህ መናፍስት ውስጥ ‹‹ቦረንትቻ›› (የቦረና ኦሮሞ መንፈስ) እና ‹‹አቴቴ›› ይገኙበታል። የአማራ ክርስቲያኖች ከነዚህ መናፍስት የተወሰኑትን ወደራሳቸው እምነት ቀላቅለዋል። ‹‹ውቃቢ›› በመባል በሰፊው የሚታወቁት አቴቴ እና አውሊያ የሚጠቀሱ ናቸው። በሰው ዘር ዙሪያ 44 አውሊያዎች ወይም መናፍስት አሉ ብለው ኦሮሞዎች ያምናሉ። በሚያስግርም ሁኔታ ይህ ቁጥር የ44ቱን ቅዱሳን ሰሞች ከያዙት ከ44ቱ ታቦታት (የ10ቱ ትእዛዛት አምሳያ ታቦቶች) ጋር የሚገጣጠም ነው።

የቦረንቲቻ አምልኮ ክርስቲያን በሆኑም ባልሆኑም ኦሮሞዎች እንዲሁም በአማሮች እና በሌሎችም ኢትዮጵያውያን በግንቦት ወር የትድስት ማርያም ልደት /ልደታ/ ተብሎ በሚታመንበት ዕለት ያከበራል። ይህን በዓል ለማክበር ሰዎች ‹‹አድባር›› በሚሉት እንደ

ቅዱስ በሚታሰብ ዛፍ ስር ይሰበሰቡና ምግብ/ንፍሮ/ ይቀቅላሉ፤ የያዙትን ስጦታም ከቅድስት ማርያም ጋር ለሚያምታቱት ለቦረንትቻው ይሰጣሉ።

አማሮች የወረሷት በጣም ታዋቂዋ የኦሮሞ ተመላኪ ‹‹አቴቴ›› ናት። ‹‹አቴቴ›› እንደ ጠባቂ መልአክ ያለች ሴት መንፈስ ስትሆን ‹‹እቴቴ ጊንቢ›› የግንብ መንፈስ፣ "አቴቴ ሓራ"፣ የሐይቅ መንፈስ እና "አቴቴ ዱላ" የጦርነት መንፈስ በሚሉ ሶስት መልኮች ትከስታለች። የአቴቴ አከባበር ስለሚረዝም አልጽፈውም።

‹‹ውቃቢ›› ወይም ‹‹አውሊያ›› የሚለው አምደ-ቃል ከረጂም ዘመን በፊት በቀጥታ ወደ አማርኛ መዝገበ ቃላት ገብቷል። ‹‹ውቃቢ ጠባቂ መልአክ ነው›› ተብሎ ስለሚገመት ሁለቱም /ኦሮሞዎችም አማሮችም/ ከውቃቢዎቹ አንዱ እንዲያድርባቸው ይመኛሉ። ለዚህ ነው አንድ ሰው ችግር ሲገጥመው አማሮች ‹‹ውቃቢ ራቀው›› የሚሉት። ‹‹ውቃቢዬ ወደደው፣ ውቃቢዬ አይወደውም›› የሚሉ አባባሎችም አሏቸው። አንዳንዶቹ ውቃቢዎች በመጨረሻው ስማቸው ላይ የኦሮሞ ስሞች አሏቸው፤ ለምሳሌ ‹‹ወስን ጋሻ›› እና ‹‹ጠቋር አባቡሌ›› የሚሉት የሚጠቀሱ ናቸው። ወንዶችና ሴቶች ውቃቢ ሲነሳባቸው ሩሓቸውን ይስታሉ፤ የውቃቢውን መንፈስ ይላበሱና በጤናማ ጊዜያቸው በማይችሉት ቋንቋና የድምጽ ቅላፄ ይናገራሉ። ውቃቢው ብዙውን ጊዜ እንስሳትንና የተለየ ቀለም ያላቸውን ዶሮዎች ጨምሮ ልዩ ልዩ ምስ ‹‹ጭዳ›› እንዲቀርብላቸው ይጠይቃሉ። ቢሆንም ከክርስቲያኖች አንፃር ውቃቢ የሰፈረበት ሰው ‹‹አጋንንት›› ወይም ‹‹ሰይጣን›› እንደያዘው ተደርጎ ነው የሚታሰበው።

በኦሮሞዎች፣ አማሮች እና በሌሎች ክርስቲያኖች በሆኑትና ባልሆኑት ኢትዮጵያውያን በጋራ የሚከበር ከዘመን መለወጫ የተለየ በዓል መስቀል ነው። ሲዳማዎች፣ ኦሮሞዎች፣ ጉራጌዎች፣ ቲጋሩዎች እና ሌሎችም ኢትዮጵያውያን መስከረም 16 እና 17 ቀን ደመራ በማቀጣጠል፣ በመጨፈር እና በመደሰት ያከብሩታል። ይህ በዓል በተከበረ በሳምንቱ ታዲያ ክርስቲያኖች እና ክርስቲያን ያልሆኑ ሌሎች ኢትዮጵያዊያን ‹‹ኢሬቻ›› የተባለ የኦሮሞ በዓል ከአዲስ አበባ ብዙም ሳይርቅ ቢሾፍቱ (ደብረዘይት) ወይም ሌላ ስፍራ ያከብራሉ።





ኢሬቻ ሙሉ በሙሉ በየዐመቱ እግዚአብሄርን የማመስገኛ የኦሮሞ ሃይማኖታዊ ዐመትበዐል ነው። ከረምቱ ወጥቶ ዐዲሱ ዐመት መስከረም ሲጠባ እግዚአብሄር ከዘመን ዘመን በሰላምና በብልጽግና ስለአደረሳቸው ህዝቡ ያወድሱታል። በሸዋ በዐሉ በሚከበርበት ዕለት ከአካባቢውና ከሌሎችም ቦታዎች የተሰያዩ ኢትዮጵያዊያን ወደ በዓሉ ማክበሪያ ቦታ /ደብረዘይት ሆራ ሓይቅ/ ይተምማሉ። በሆራ ሓይቅ መግቢያ ላይ በሬ ይታረዳል። አንዲት በህዝቡ የምትከበር እና የምትፈራ ሴት በውሃው ዳር ቆማ ካመሰገነች እና ከፀለየች በኋላ የበዓሉን ታዲሚዎች በመመረቅ የበአሉን ሥነ ሥርዓት ታከናውናለች። ለምሳሌ መካን ሴቶች በረከቷን ለማግኘት እፊቷ ያጎነብሳሉ። እሷም ቄጤማ ወደ ሓይቁ ውስጥ ነክራ ትፀልይና ለሚቀጥለው ዓመት ሌላ እሬቻ ለማከናወን እንደሚመጡ፤ ሲመጡ ታዲያ ልጅ ወልደውና ታቅፈው እንደሚሆን እየተነበየች በቄጤማው የጠቀሰችውን ውሃ አጉንብሰው ምርቃቷን በሚለምኑት መካን ሴቶች ላይ ትረጭባቸዋለች። አባገዳውም እንዲሁ ዋቃ የተባለውን እግዚአብሄርን አመስግኖ የተለመደውን ስርዐት ካከናወነ በሁዋላ የእሬቻው በዓል ከመፈፀሙ በፊት የበዓሉ ታዳሚዎች በዛፍ ጥላ ስር ይሰበሰባሉ። ይህን የሚያደርጉትም በዋቃ ለመባረክ እንደሆነ ያምናሉ። በዛፉም ስር ልዩ ልዩ ስጦታዎችን ያስቀምጣሉ፣ ሉቲ/አዲስ ጨርቅ/ ዛፉን አልብሰው ያስጌጡታል።

የአቴቴ አምልኮን፣ የውቃቢን እና የኢሬቻን በዓላት የሚያከብሩትን አማሮች ከግምት ውስጥ ስናስገባና ባጠቃላይ ክርስቲያኖች በተለይ ደግሞ አማሮች መሆናቸውን ስናይ በኦሮሞ ሃይማኖት በአያሌው መሳባቸውን እንገነዘባለን።

ያንድ ሰው ዋናው እሉነት መንፈሱ ወይም ኅሲናው በመሆኑ ጥልቁ የአማራ ውስጣዊ ማንነት በኦሮሞ ሥነ-ልቦና የተሞላ ነው። በገሃዱ እውነታ እንዲህ ዓይነቱ የመንፈስ ውህደት ደግሞ ከስር መሠረቱ ኦሮሞና አማራ ካላቸው የሥጋ ዝምድና የበለጠ ይጠነክራል። ምክንያቱም መንፈስ ሥጋን ያዛልና። ሁለቱንም፤ መንፈስንም ሥጋንም ከግምት ውስጡ ስናስገባ ደግሞ ኦሮሞና አማራ ካንድ እናትና አባት ስለፈለቁ እና ላለፉት 3500 ዓመታት በኢትዮጵያ አገራቸው ውስጥ አብረው አንድ ላይ ስለኖሩ በመንፈስ፣ በደም እና

በሥጋም አንድ ሆነዋል። ስለዚህም እነዚህን ሕዝቦች የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ሲባል ለመከፋፈል መሞከር እርባና ቢስነት ነው።

እሮሞዎች በአማሮች ላይ ይህን መሳይ ተፅእኖ እንዳሳደሩ ሁሉ በአፀፋው ደግሞ አማሮችም በኦሮሞዎች ላይ የቋንቋ፣ የባህል እና የሃይማኖት ተጽእኖ አሳድረዋል። በመሆኑም አንዳንዶቹ ኦሮሞዎች ወደ ክርስትና እምነት ተሰውጠው የግዕዝ እና የአማርኛ ቋንቋዎች ተናጋሪ ሆነው በየዕለቱ ውሎ አዳራቸው የአማራን የአኗኗር ልማድ ይዘዋል። የኦሮምኛ ቋንቋ በአማርኛ ቃላት ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ አባባሎች እና ተረታ ተረቶች በልጽጓል።

## ለውትድርና ሳይንስ አስተዋጽኦ

ኦሮሞዎች እስካለፉት 350 ዓመታት ድረስ ፈረሶችን ለጦርነት መጠቀም አልጀመሩም ይሆናል። ከኦሮሞዎች በፊት አማሮች እና ቲጋሩዎች ነበሩ ፈረስን ለጦርነት የሚጠቀሙበት። ሆኖም ኦሮሞዎች እንስሳትንና ተፈጥሮን የሚወዱ በመሆናቸው ፈረሶቻቸውንና ሌሎችንም ለማዳ እንስሳዎቻቸውን ስንኝ እየቋጠሩ እና ዜማ እየደረሱ በግጥም እና በመዝሙር ሳይቀር ያሞግሷቸዋል።

ኦሮሞዎች ፈረሶችን ለጦርነት መጠቀም ከጀመሩ በኋላ የፈረስ ግልቢያን ወደ ጥበብነት አሳድገውታል። ቀስ በቀስም የተራቀቁ ፈረስ ጋላቢዎች እና ጦረኞች ሆነዋል። ‹‹ጉግስ›› የተባለ የፈረስ ላይ ጨዋታና ውድድርም ፈጥረዋል። የጉግስ ጨዋታ ክዋኔ ሦስት ደረጃዎች አሉት፤ ‹‹ሶምሶማ›› ፈረሱን በቀስታ እና በግርማ እያስደነሱ ማስኬድ፤ ‹‹ደንገላሳ›› ከሶምሶማ ፈጠን አስደርጎ ፈረሱን በምታዊ/Rythmic/ ስልት ማስጨፈር እና ‹‹ሽምጥ›› ፈረሉ ሙሉ ሃይሉን ተጠቅሞ በከፍተኛ ፍጥነት እንዲበር እና ተወዳዳሪውን እንዲቀድም ወይም ከጠላቱ እንዲያመልጥ ወይም በጠላቱ ላይ እንዲደርስበት ማስቻል ናቸው።





የአማራ የጦር መሪዎች እነዚህን የፈረስ ግልቢያ ስልቶች ስለሚወዷቸው ይጠቀሙባቸው ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ አማሮች የኦሮሞን የፈረስ አገራር በጣም ይወዱታል።

‹‹ወርዶፋ ጨንገሬ እንደገራው ፈረስ፤

‹‹ጡቷ ደንገላሳ ይላል መሰስ ቀሰስ››

እየሱ አንደ እራስ ነብር አትንኩኝ የሚለውን የሴቷን ጡት እንቅስቃሴ ውበት በወርዶፋ ጨንገሬ ከተገራው ስልጡን ፈረስ የደንገላሳ ስልታዊ እንቅስቃሴ ማራኪነት ጋር በማነፃፀር ያሞገሱበት ሕዝባዊ ግጥም በአማርኛ ሥነ-ቃል ውስጥ ይገኛል። (ካሣ ተሰማ የተባለው ተወዳጅ ድምፃዊም አዚሞታል)። ወርዶፋ ጨንገሬ በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በጨፌ-ዶንሳ አካባቢ ፈረስ እያረባ፣ እየገራና እየሸጠ የሚኖር፤ በሚገራቸው ፈረሶች ብቃትና ታዋቂነትን ያተረፈ ስመ-ጥር ፈረሰኛ ነበር።

ሌላ ኦሮሞዎች ለአማሮች ያስተዋወቁት የጦርነት ጨዋታ "አኮንዱራ" የሚለው ነው። ፍቺው ምናልባት ‹‹በጥንት ጊዜያት›› የሚል ይሆናል። ይህ ጨዋታ ከሌሎቹ ጨዋታዎች ለየት ባለ መልክ በልጆች እና በወጣት ወንዶች ይከናወናል። አጥንት እና ስንጥር እንጨት እንደ ኣረር ይዘው፣ ጎራ ለይተው፣ ጦርነት በማስመሰል ይጫወታሉ። ወደፊት ጦረኞች ይሆኑ ዘንድ ራሳቸውን ለማብቃት የሚጫወቱት ጨዋታ ነው።

ሌላው ኦሮሞዎች ለኢትዮጵያ የጦርነት እቅድ ያበረከቱት ስልት በጭፍራ የመዋጋትን ዘዴ ነው። በንጉሥ ሱስንዮስ ዜና መዋዕል ውስጥ እሮሞዎች ራሳቸውን በጭፍራ ከፋፍለው እንዴት ከአማሮች ጋር እንደተዋጉ ተጽፏል።

የኢትዮጵያ የጦር መሪዎች ለፈረሶቻቸው የስጧቸው ስሞች ሲታዩ ሁሉም ‹‹አባ›› የሚለው የእሮምኛው ቅድመ-ግንድ ቅጥያ ምሳሌ አላቸው። በኦሮምኛ "አባ" ማለት አባት ወይም ባለቤት ማለት ነው። የኦሮሞ ባላባቶች ለፈረሶቻቸው በዚህ ዓይነት መንገድ ስም

የማውጣት ልማድ ነበራቸው፡፡ ከጊዜ በሁዋላ የአማራ አልፎም የትግሬዎች ሹማምንት እና ጦረኞች ፈረሶቻቸውንና ራሳቸውን በዚህ በኦሮሞ ልማድ መጥራት ጀመሩ፡፡ ብዙውን ጊዜ የፈረሶቹ ስሞች የፈረሱ ጌታ እንዲታወቅበት የሚፈልገውን ጠባይ የሚያንፀባርቁ ነበሩ፡፡ በዚህም በፈረሶቹ ስሞች ሰዎቹም ተለይተው ይታወቁባቸው ነበር፡፡ ለምሳሌ የዳግማዊ ምኒልክ አያት የነበሩት የሸዋው ሣህለ-ሥላሴ በፈረሳቸው ስም "አባዲና" ተብለው ይጠሩ ነበር፡፡ በኦሮምኛ "አባዲና" ማለት ድንገት የሚወር አስፈሪ ጠላት አባት ማለት ነው፡፡ የባለቤቶቹም መጠሪያዎች የሆኑት ጥቂት የፈረስ ስሞችን ልጥቀስ፡-

አባ ታጠቅ……. አፄ ቴዎድሮስ

አባ ዳኘ………. አፈንጉስ ነሲቡ ዛማኔል

አባ ግርሻ……….ራስ ዳርጌ

አባ ድልድል…….ራስ ዘውዱ

አባ ዳምጠው……ንጉሥ ኃይለመለኮት

አባ ትኩ…………ራስ ጉበና

አባ ጤና ………ልጅ ኢያሱ

አባ ጠጣው………ራስ ወሌ

አባ ኩራን…………ደጃዝማች ዘውዱ

አባ መቻል (አባ መላ)….ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ

አባ ነጋ……………ራስ አሉላ (የትግሬው)

አባ ነፍሶ………….ደጃዝማች ባልቻ

አባ ቃኘው……….ልዑል ራስ መኮንን እና





አባ ጠቅል……….አፄ ኃይለሥላሴ ይጠቀሳሉ፡፡

አለቃ አፅመ ጊዮርጊስ *የጋላ ታሪክ* እና *የሸዋ ስርወ መንግሥት* በተሰኙ መጽሐፋቸው ውስጥ እንደጠቀሱት አማሮች ጋሻቸውን የማስጌጥ ብልሃት ከኦሮሞዎች ተምረዋል፡፡ እስከ ዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ፍፃሜ እና እስካሁኑ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ ለአማሮች እና ለሌሎች ኢትዮጵያውያን ወታደሮች ይሰጡ ከነበሩ በርካታ የጦር የማዕረግ ስሞች ውስጥ ከኦሮምኛ የተወሰዱ አሉ፡፡ ለምሳሌ መንጫ፣ ቢተዋ፣ ከለቻ እና ማልዳያ ይጠቀሳሉ፡፡ (3)

## ለትምህርት እና ለቅኔ /የግዕዝ ሥነ-ቃል ግጥም/ የተደረገ አስተዋጽኦ

ኦሮሞዎች የሆኑ የቤተ ክህነት ምሁራን ለኢትዮጵያ ባሕላዊ ትምህርት እና ለቅኔ ጠቃሚ ድርሻ አበርክተዋል፡፡ ከጥንት ጀምሮ በኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እየሰሰጡ ያገለገሉ በርካታ ዝነኛ የኦሮሞ ደብተራዎች፣ ሊቃውንትና ቀሳውስት ነበሩ፡፡ እነዚህ የኦሮሞ ምሁራን ምርጥ ችሎታ ያላቸው የግዕዝ ሥነ ግጥም /ቅኔ/ እና የሥነ መለኮት ሊቃውንት ነበሩ፡፡ የግል ቅኔ በማስተማር ብቻ ሳይሆን ራሳቸውም በግዕዝ የቅኔ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ቅኔዎችን በመቀኘትም አገልግለዋል፡፡ የሚከተሉትን ብቻ ለአብነት እጠቅሳለሁ፡-

የሰላሌው ስሬ መድሃኒዓለም ቤተክርስቲያን ስሙ-ጥር አለቃ ጥበቡ ገኔ፤ የታዋቂው ገጣሚና ሰዓሊ የገብረ ክርስቶስ ወላጅ አባት፣ የሐረሩ ቤተክርስቲያን ስሙ-ጥር አለቃ ደስታ ነገዎ፤ የጉጃም ጫቢ ማርያም ስሙ-ጥር መሪጌታ ወልዴ እና የአቡነ ማርቆስ ዋና ፀሐፊ የነበሩት የሸዋው ስሙ-ጥር መሪጌታ ከበደ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

የግዕዝ ቀሳውስት፣ ገጣሚያንና ሊቃውንት የነበሩ የጉጃም ኦሮሞዎች በርካታ ናቸው፡፡ የኦሮሞ ምንጩ ጉጃም ስለሆነ ይህ ይህን ያህል አያስገርምም፡፡ አንዳንድ ያላወቁ የኦሮሞ ልጆች የግእዝ ሊቃዉንትና ደብተሮች አማሮች ብቻ ይመስሏቸዋል፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው በርካታ ኦሮሞዎችም የግዕዝ ሊቃውንትና ደብተሮች እንደነበሩ ልብ ይሏል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ አዲስ አበባ የሚገኘው

ቀጨኔ መድኃኒአለም ቤተክርስቲያን ባሁኑ ጊዜ በኦሮሞ ካህናትና ደበተሮች የተሞላ ነው፡፡

## ለዳንኪራ እና ለሙዚቃ የተደረገ አስተዋጽኦ

ኦሮሞዎች ማራኪ ጭፈራዎችን፣ ግጥሞችንና ስሜት የሚነኩ ጥዑም ዜማዎችን በማመንጨት የኢትዮጵያን የሙዚቃ ጥበብ በእጅጉ አበልፅገዋል፡፡ ጭፈራዎቻቸው እና ግጥሞቻቸው ፍቅርንና ከወቅቶች ጋር ተያይዞ ተፈጥሮ የሚያደርገውን ለውጥ የሚገልፁ ናቸው፡፡ በጭፈራ ወቅት ለክብረ በዓላት ተብሎ በሕብረ ቀለማት ተውበው የተዘጋጁ አልባሳትን ይለብሳሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ምት/rhythm/ ያለው ጭፈራ እየጨፈሩ እና ትከሻቸውንና አንገታቸውን በስልት እያንቀሳቀሱ እንዳንዴ ደግሞ ስለ ፍቅር ሲዘፍኑ ሰውነታቸውን ላላ አድርገው ወደ ቀኝና ወደ ግራ በመዝመም ማራኪ ስልት እየፈጠሩ ይጫወታሉ፡፡ እጅግ ተወዳጅ የሆነው ጭፈራቸው ‹‹ሸጎዬ›› የተሰኘው ነው፡፡

ይህ ጭፈራ ለየት ባለ ሁኔታ ምናልባትም ባመት አንድ ጊዜ ወጣቶች ለፍቅር ሲቀጣጠሩ የሚጨፈር ሲሆን በተለይ በሐረር እና በወሎ ኦሮሞ ዘንድ በጣም ተወዳጅ ነው፡፡ ሸጎዬን የሐረር ኦሮሞዎች በኦሮምኛ ሲዘፍኑት በሚገርም ሁኔታ የወሎ ኦሮሞዎች ደግሞ በአማርኛ ይጫወቱታል፡፡ በሸጎዬ ጨዋታ ወቅት ወጣት ወንዶች እና ልጃገረዶች ሎሚ በመወርወር ወይም ልጃገረዶቹ የሚፈቅዱት ወጣት ለዚሁ ሲል በያዘው ሽል ዱላ ጫፍ ላይ ሎሚውን በመሰካት ለፍቅር ይመራረጣሉ፡፡ አንዳቸው ባንዳቸው ላይ ሎሚ በመጣል የፍቅር ምርጫን የመግለጽ ባሕል በተወሰኑ አማሮች ዘንድም አለ፡፡ ከኦሮሞ የወረሱት ሳይሆን አይቀርም፡፡

## የሙዚቃ መሣሪያዎችን በተመለከተ

ከአማራ፣ ከትግሬና ከሌሎችም ጋር ከሚጋሩት ከማሲንቆ እና ከራር በተጨማሪ ኦሮሞዎች ከኩንቢ እና ከቆዳ የተሰሩ እንደ ከበሮ እና ዋሽንት ያሉ የራሳቸው የሙዚቃ መሣሪያዎች አሏቸው፡፡





# ልዩ ልዩ አስተዋጽኦዎች

### የንድፍ ጥበብን በተመለከተ

የበቾ፣ እኒያ፣ ሌቃ፣ ሸዋ፣ ሜጫ፣ ወለጋ እና ጂማ ኦሮሞዎች ለምሳሌ የእንዱ ቤት ከአንዱ እንዲለይ አድርገው እና በንድፍ ጥበብ አራቅቀው የየራሳቸውን ቤት ንድፍ አውጥተው ይሠራሉ፡፡ ይህ ሁሉ የተለያዩ የቤት አሠራር ቅርፀ-መልክ አንድ ላይ ሲወሰድ ለኢትዮጵያ ልዩ የንድፍ ጥበብ የራሱን ድርሻ ያበረክታል፡፡ ከነዚህ ቤቶች ውስጥ አንዳንዶቹ አቀሳለሳቸው አማሮች የሚሠሯቸውን ቤቶች ስለሚመስሉ ኦሮሞና አማራ ጥበብን እርስ በርስ መቀላለሳቸው ግልጽ ነው፡፡

ከዕደ-ጥበብ ጋር በተገናኘ ኦሮሞዎች የተለያዩ የቤት ቁሳቁሶችን አበርክተዋል፡፡ ለምሳሌ በርጩማ፣ የፀጉር ማበጠሪያዎች፣ ትራሶች፣ የተዋቡ ቅሎች እና ከሰምና ከሞራ የተሠሩ መብራቶች ይገኙበታል፡፡ በተጨማሪም ኦሮሞዎች እንደ ወርቅ፣ ብር፣ አልቦ፣ እምባር እና ሐብል የመሳሰሉ የመዋቢያ ጌጣጌጦችን ይሠራሉ፡፡ ሸማኔዎቻቸውም ቡሉኮ እና ጋቢ ከጥጥ ፈትል ይሸምናሉ ፡፡ አማሮች ጸጉራቸውን ቅቤ መቀባት የተማሩት ከኦሮሞዎች ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ኦሮሞዎች የእንስሳት ተዋፅኦ በአያሌው ከመጠቀማቸውም በላይ ሰውነታቸውን እና ፀጉራቸውን አብዝተው ቅቤ ስሚቀቡ ነው፡፡ ቅቤ ቆዳን እና ጸጉርን ከማለስለሱም ባሻገር ከባድ የራስ ህመምን ያሸላል፡፡ ኦሮሞዎች ድንቅ የሆኑ የሴት ፀጉር አሠራር ብልሀቶችን ለኢትዮጵያ ባህል አስተዋውቀዋል፡፡ የአርሲ፣ የሐረር፣ የወለጋ፣ የሜጫ፣ የጅማ እና የሊሙ ኦሮሞዎች ብቻ በአጭር ከሚቆረጠው በረጅም እስከሚለቀቀው ድረስ ቢያንስ 7 ዓይነት የባርኔጣ ቅርፅ ያላቸው እፁብ ድንቅ የአሰራር ብልሃቶች አሏቸው፡፡

የኢትዮጵያ ኦሮሞዎች እነሱን እና እንስሳቶቻቸውን ካሳደገው እና ከጠለለው ተፈጥሮ ጋር ቅርበትና ስምምነት ስላላቸው እያንዳንዱን እስ ለይተው ስም አውጥተውለታል፡፡ እንዳንዶቹንም ለመድኃኒትነት ይጠቀሙበታል፡፡ አማራው እና ሌላውም ኢትዮጵያዊ እፅዋቱን

ኦሮሞዎች ባወጡላቸው ስያሜ ይጠሯቸዋል። ኦሮሞዎቹ እንደሚያደርጉትም ይታከሙባቸዋል።

በአትሌቲክሱ መስክ ደግሞ እንደ አበበ ቢቂላ፣ ዋሚ ቢራቱ፣ ኃይሌ ገብረሥላሴ፣ ቀነኒሳ በቀለ፣ እሸቱ ቱራ፣ ቶሎሳ ቆቱ፣ ደራርቱ ቱሉ፣ ጥሩነሽ ዲባባን እና የመሳሰሉትን መጥቀስ በቂ ነው። እነዚህ ብርቅዬ ልጆቿ በዓለም እና በኦሎምፒክ ውድድሮች ሻምፒዮኖች እየሆኑ እናት አገራቸውን ኢትዮጵያን በእጅጉ አኩርተዋታል።

ለኢትዮጵያ ነፃነት እና ስልጣኔም የኦሮሞ አስተዋፅኦ ግዙፍ ነው። የኦሮሞ ጀግኖች በ1896 ዓ.ም በአድዋ ጦርነት እና በ1936 ዓ.ም የፋሽስት ወረራ ከጣሊያኖች ጋር በከፍተኛ ጀብዱ ተዋግተዋል። ኢትዮጵያ በአድዋ ጦርነት የተጎናፀፈችው ድል በኢምፔሪያሊዝም ተጨቁነው እና በባርነት ተግዘው በመላው ዓለም የነበሩ ነጭ ያልሆኑ ህዝቦችም ያገኙትን ድል የሚወክል ነው።

ከጀግኖች አባቶቻችን እና በጦርነቱ ቦታ ተገኝተው ተዋጊዎቹን ከመገቡትና እና የቆሰሉትን ከአከሙት እናቶቻችን በተጨማሪ ለድል የበቃነው በአፄ ምኒልክ እና የኦሮሞ ዝርያ በአለባቸው በቆራጥዋ ባለቤታቸው በእቴጌ ጣይቱ ብጡል ወሌ አቀነባባሪነትና ተሳትፎ ስለሆነ ሁለቱም መወደስ ይገባቸዋል። እነሱ ተዋግተውና አዋግተው ከጣልያን ባርነት ባያተርፉን ኖሮ በቅኝ እንደተገዙት ህዝቦች ሁሉ ቅስማችን ተሰብሮ የዝቅተኛነት ስሜት እያጠቃን እንገታችንን በደፋን ነበር። ደግሞም ዛሬ ደረታችንን ነፍተን በኩራት ባልተራመድን ነበር። ጣልያን ከ40 ዐመታት በሁዋላ ለበቀል መጥቶ ከተማ ከተማውን ለ 5 ዐመታት በተቆጣጠረ ጊዜ ኢትዮጵያን 5 ቦታ ከፍሎ ሲገዛት ሞክሮአል። አማራ፥ ኦሮሞ፥ ሀረሪ፥ ሲዳማ እና ኤርትራ ብሎ። ቶሎ አሰለቅቀን ባናባርረው ኖሮ እንደዛ በማድረጉ በሀረር፥ በባሌ፥ በአሩሲ፥ በወለጋ እና ሸዋ የሚኖሩት ኦሮሞዎች ሁሉ እንደ አማሮቹ ወገኖቻቸው ተለያይተው ሳይገናኙ ተዋርደው ቅስማቸው ተሰብሮ በቀሩ ነበር። የአድዋ ድል እና የሁለተኛውም ጦርነት አሸናፊነታችን ባስገኘው አንድነት ስር ቆይተን ባንደራጅ ኖሮ ዛሬ ኦሮሞዎችም ሆንን አማሮች ወይም ተጋሩዎች ርስ በርሳችን አሰን የምንለው አንድነት ጠፍቶ ብትንትናችን ወጥቶ ከነ ኩራታችን የውሃ ሽታ በሆንን ነበር። ከአድዋና ከ ፋሺሽቱ ወረራ ድል በሁዋላ በተገኘው ነፃነትና አንድነት





ስር በመቆየታችን ግን እስከ ዛሬ ለመሰባሰብና በማንነታችን ለመተማመን በቅተናል።

ኦሮሞዎች በሁለቱም ጦርነቶች ከወንድሞቻቸው ከአማሮች እና ከሌሎችም ኢትዮጵያዊያን ጋር እንድ ላይ ሆነው የእናት አገራቸውን ነፃነት ለማስከበር ከአረመኔዎቹ የአውሮፓ ቀኝ ገዢዎች ጋር በጀግንነት ተዋግተዋል። ለአብነት የሚከተሉትን ታላላቅ አርበኞች ማንሳት ይበቃል። የወሎው ራስ ሚካኤል ምንም የመሃመድ ልጅ ቢሆኑም ከ1600 አረሞ ወታደሮቻቸው ጋር 1000ዎቹ ፈረሰኞች የነበሩ፤ ፊትአውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ እና ደጃዝማች ባልቻ አባነፍሶ እንዲሁም ከ40 ዓመት በሁዋላ በፋሺሽት ኢጣሊያ ወረራ ወቅት ደግሞ ደጃዝማች ገረሱ ዱኪ፣ ደጃዝማች ገርቢ ቡልቶ፣ ኮሎኔል አብዲሳ አጋ፣ ጀኔራል ሙሉጌታ ቡሊ እና ጀኔራል ጃጋማ ኬሎ ሰኢትዮጵያ ነጻነት በጀግንነት የተዋጉ ስመጥር አርበኞች ናቸው። በነፃነቱና ለላሙም ዘመን የሀገራቸውን ዳር ድንበር ሲያስከብሩ ኖረዋል።

ወደ ጥንቱ ባንሄድ እንኳ ከ12ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ ብቻ ፖለቲካን፣ ውትድርናን፣ ትምህርትን፣ ባህልን እንዲሁም ሥነ-ጥበብን እና ሥነ-ጽሑፍን ጨምሮ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥታት ውስጥ ኦሮሞዎች ቁልፍ ቦታዎች ነበራቸው። እነዚህን በተገቢው ቦታና ጊዜአቸው በዝርዝር አነሳለሁ። ከላይ ከቀረቡት መረጃዎች እንደምንረዳው ፕሮፌሰር ኤ. ኡሉንዶርፍ ከፃፉት በተቃራኒው ኦሮሞዎች ለኢትዮጵያ ስልጣኔ ግዙፍ አስተዋፅኦ አበርክተዋል። በተጨማሪም የታላቅ አእምሮአዊ እና ቁሳዊ ባህል ባለቤቶችም ናቸው። ይህ ሲባል ታዲያ አማራው ለኦሮሞ ባህል ያበረከተው የለም ማለት አይደለም። ቀደም ሲል እንደተገለፀው የሁለት ወገን መበዳደር፣ መዋዋስ፣ መወራረስ ነው የነበረው።

አማራም እንዲሁ በመቶዎች በሚቆጠሩ እመታት ውስጥ በርካታ ቃላትን ለኦሮምኛ ቋንቋ በማዋስ የኦሮምኛን መዝገበ ቃላት አበልፅጓል። ይህን አባባሌን በሚከተለው ማስረጃ አስደግፋለሁ። ኢትዮጵያ ውስጥ ይኖሩ በነበሩ ሬቭ.ጄ.ኤል.ክራፕፍ በተባሉ የጀርመን ሚሲዮናዊ "የኦሮሞ ቋንቋ መዝገበ ቃላት" በሚል ርእስ ከ200 ዓመት በፊት የተዘጋጀ አንድ መዝገበ ቃላት አለ። *Vocabulary of the*

*Oromo Language*, by the Rev. J.L. Krapf (4). በዚህ መዝገበ ቃላት ውስጥ በእያንዳንዱ ገፅ ቢያንስ ሁለት አማርኛ የነበሩ እና በጊዜ ሂደት ኦሮምኛ የሆኑ ቃላት ይገኛሉ። ጥቂቶቹን፣ ማለትም ከኤ እስከ ጂ ባሉት ቅደም ተከተሎች ውስጥ ያሉትን በመጀመሪያ አገልፃለሁ። ቀጥሎም ከኤች እስከ ዜድ ያሉትን ቃላት። ቅደም ተከተሉ መጀመሪያ አማርኛ ቀጥሎ ኦሮምኛ ነው።

ገባሪ gebabri, ምልክት melekita, በረከት bereketa, ስስት sesitu, መጥረቢያ matrabya or kotto, ካስ quasi, ሚዛን mitshana, ገረፈ garafe, አረር arari, መረጠ marate, ጥምቀት temkata, መስቀል meskela, ማረ mare, አተላ atala, ወስን wassana, ምክንያት mekniata, ሬሳ ressa, መረገ marige, ዋንጫ wantsha, ቅዱስ kedusi, ቀደደ kadade, ወሰነ wassani, ተንኮል tankolli, ተበደረ beddere, ለዳ ida, ሳጥን satini, ቆፈረ koffere, ልጓም leguama, ማዕረግ maragi, ቱካና tukana, ተማሪ tamari, ቆብ kobi, ወጭት wochitti, ቁልፍ kulfi, ፈተና fatana, ፈጋራ fagara, ሊጥሮ litti, ሰንሰለት senselata, ጓዳ guada, ከሰለ kessela, ወባ woba, ሞረድ morada, አጠመደ tsamade, ፆም tsoma, ግድ giddi, ብርጭቆ bertsheko.

ፍላጎቴ ኦሮምኛ የሆኑ የአማርኛ ቃላትን በሙሉ መዘርዘር ስላልሆነ ከላይ የሚገኙትን ብቻ ጠቀስኩ። እነዚህ እንግዲህ ቀደም ሲል እንደገለፅኩት ከ200 ዓመታት በፊት የነበሩ ናቸው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮም ኦሮምኛ ቋንቋ በርካታ አማርኛ ቃላትን ወርሶ ወደ መዝገበ ቃላቱ ቀላቅሏል። አማርኛ እና ኦሮምኛ ቋንቋዎች አንዳቸው ለአንዳቸው ያበረከቱትን አስተዋፅኦ በትክክል ለማወቅ የበለጠ ጥናት ማካሄድ ያስፈልጋል። እንደ እውነቱ ከሆነ የሁሉም የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ቋንቋዎችና ባሕሎች የእርስ በርስ መወራረስ በወጉ መጠናት እና ለህዝቦቻችን አንድነት መሰረት የሆኑት ሁኔታዎች በውል ተለይተው መታወቅ አለባቸው። ይህ ሲደረግ ፍቅር፣ መግባባት፣ ውህደት እና አንድነት በሁሉም የኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል ይሰፍናል።

ከላይ እንደተመለከትነው የኦሮሞ ባህልና ቋንቋ ከራሱ አልፎ ተርፎ ወደ አማራና ሌሎች ኢትዮጵያውያን ተላለፈ እንጂ ዳብዛው





አልጠፋም። የኦሮምኛ ቋንቋዋና ባህል ታፈነ ወይም ሳይስፋፋ ቀረ የሚለው አነጋገር መሰረት የለውም። ትልቁ የኦሮሞ ህዝብ ቋንቋዋና ባህሉ በይፋ እንዲያንሰራፋ በመንግሥታት በጮክታ ባይታወጅለትም፥ ከአማሮችም ሆነ ሌሎች ህዝብ ጋር በደም፥ በንግድና በማህበራዊ ጉዳይ ሲገናኝ በመኖሩ ቋንቋውና ባህሉ በብዙሃን ኢትዮጵያውያን ውስጥ ስር ሰዶ ባንድም ሆነ በሌላ መልኩ ከአፅናፍ እስከ አፅናፍ ተንሰራፍቶአል። ይህ የማይካድ ሃቅ ነው። አስተዋይ አእምሮ ሁሉ ይህን ሊያጤን ይችላል።

# አመላካች (Notes):

## Oromo Contribution to Ethiopian Civilization

1. E.Ullendorf, *The Ethiopians*, p.7.

Cotter, George, Proverbs and Sayings of the Oromo Peoples of Ethiopia and

*Kenya,* pp,. 5-20

3. Bairu Tafla, ed. *Asma Giyorgis and His Work*, p.p. 170-171

4. The Rev. J.L. Krapf, *Vocabulary of the Oromo Language* pp. 1— 42





# ክፍል ሁለት

## የኦሮሞና የአማራ ሕዝብ እውነተኛው ዘር ምንጭ

የኢትዮጵያ ኦሮሞዎች በርግጥ ከውጪ ፈልሰው የመጡ ወራሪዎች ናቸው ወይስ ነባር የኢትዮጵያ ልጆች?

ኦሮሞዎች ከውጪ መጥተው ቢሆን እንኳ "ወደ ኢትዮጵያ አቀኑ" በሚባልበት ትክክለኛ ጊዜ ላይ የኦሮሞ ታሪክ አዋቂዎችን ጨምሮ ስለ ኦሮሞ የጻፉ በርካታ ምሁራን አንድ ዓይነት ስምምነት የላቸውም፡፡ ሁሉም በደፈናው ከውጪ መጡ በሚለው መንደርደሪያ ላይ ብቻ ይስማማሉ፡፡

ስለ ኦሮሞ ምንጭ አንዳች ከሰነዘሩ ዋና ዋና ጸሓፍትና ባለታሪኮች መካከል ጥቂቶቹን ልጥቀስ፡-

በ16ኛው ክፍለ-ዘመን የነበሩ አባ ባሕርይ የተባሉ መነኩሴ *‹‹..በአፄ ወናግ-ሰገድ ዘመን (1500-1533) (ጋላ) ከምእራብ ወጥቶ ጎላና የሚሉትን የሀገሩን ወንዝ ተከትሎ ወደ ባሊ (ባሌ) ዳርቻ ተሻገረ፡፡ እሉም በረይቱማና ቦረን የሚባሉ ሁለት ነገድ (ወንድማማች) ነው፡፡ በረይቱማ ስድስት ልጆች ይወልዳል፡፡ በኩሩ ከረዩ ይባላል፣ ሁለተኛው መረዋ፣ ሦስተኛው ኢቱ፣ አራተኛው አከቹ፣ አምስተኛው ወረንቢሻ፣ ስድስተኛው ሁምበና ይባላሉ፡፡ ቦረኖች አባታቸው ሰጺራ ይባላል፡፡ ሰጺራ ዳጬን ይወልዳል፤ ዳጬ ሜጫን ይወልዳል፤ ሜጫ ደኣሌን እና ጂዳን ይወልዳል፡፡ (እነዚህ) ሁለቱ ወንድማማቾች ብዙዎች ነገዶችን ወለዱ፡፡ እነሱም የደኣሌ ልጆች (እነ) ሆኮ፣ ሁለተኛ ጭሌ፣*

ሶስተኛ ኣቦ፣ አራተኛ ሱባ ናቸው። ጂዳ በኩሩን ሃካክን፣ ሁለተኛውን ጉድሩን፣ ሦስተኛውን ሊበንን ይወልዳል››(1) በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ-ዘመን በዳግማዊ አጼ ምኒልክ ዘመነ-መንግሥት የነበሩ አለቃ አጽመ-ጊዮርጊስ የተባሉ ጸሐፊ ደግሞ ስለ ኦሮሞ አመጣጥ ለጻፉት ምንጫቸው የአፄ ሱስንዮስ ዜና መዋዕል ጸሓፊ የነበሩ አዛዥ ጢኖ የተባሉ የኦሮሞ ደብተራ መሆናቸውን ቢገልጹም (2)ፕሮፌሰር ባሕሩ ታፍሳ አጽመ-ጊዮርጊስ እና ሥራቸው በተሰኘ መጽሐፋቸው የግርጌ ማታወሻ ላይ አዛዥ ጢኖ ስለ ኦሮሞ አመጣጥ እንዳልጻፉ አረጋግጠዋል።(3) አዛዥ ጢኖ እንደጻፉ ተደርጎ በአለቃ አጽመ-ጊዮርጊስ መታሰቡ ስህተት መሆን አለበት። አለቃ አጽመ-ጊዮርጊስ ስለ ኦሮሞ አመጣጥ የጻፉት እንደሚከተለው ነው፡-

‹‹አውሮጳውያን ምርምራቸውን መሰረት አድርገው ሆን ብለው ጽፈዋል። እኛ ደግሞ አዛዥ ጢኖን መሰረት አድርገን እንጽፋለን። ጋሎች የገላንን ወንዝ ተከትለው መጡና ከላይ እንዳተትነው ወላቦ ወደተባለ አገር ገቡ። በሓሮ ወላቦ ሰው የሚዋኝባት ኣንዲት ትንሽ ሓይቅ አለች። ከዚያች ውሃ ሰው እና እንስሳ መጠጣት ክልከል ነው። ጋሎች በሙሉ ውሃውን እያመሰኩ አያሌ ላሞች፣ በጎች እና ፍየሎች ይሰዋሉ። በቃል-ትውፊት መሰረት ጋሎች ያልተሰመደ አዲስ ነገር ሲያጋጥማቸው እንደሚከተለው ይላሉ፡- ‹‹ኤርጋ ዱፍታን ዱፍቴ ኡሜን ወላቡ ባቴ። ዱቢ ኣካና ኢርገኔ ሀንቤክ›› ፍችው “ህይወት (ፍጥረት)ከ ውላቦ ውሃ ከወጣች ጀምሮ፤ እንዲህ ዓይነቱን ነገር ፈጽሞ አይተን አናውቅም” ማለት ነው። (4)

አለቃ አጽመ-ጊዮርጊስ በመቀጠል፡- “እስያ የሰው ልጅ መገኛ እንደሆነ ሁሉ (የሰው ዝርያ መገኛ አፍሪካ በተለይም ኢትዮጵያ መሆንዋን የቅርብ ግኝቶች ከሚያረጋግጡት ጋር መቃረኑን ልብ ይሉዋል) የጋላን ታሪክ ስንጽፍ ከእስያ ወደ ማደጋስካር ከዚያም የገናሌን ወንዝ ተከትለው ወደ ሞምባሳ (ሞምባሳ ኬንያ) ከመፍለሳቸው እንጀምራለን” ይላሉ።(5)

አለቃ ታዬ ምንም አዲስ ነገር አያወጉንም። ‹‹ኦሮሞ የፈለሰው ...በመጀመሪያው የዛጉዬ ንጉሠ-ነገሥት በመራ ተክለሃይማኖት ዘመን እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ930 ዓመተ-ዓለም ነው›› ከማለታቸው በቀር አለቃ አጽመ-ጊዮርጊስ ያሉትን ነው ያስተጋቡት።(6)





በርካታ መጻሕፍት በመጻፍ የሚታወቁት የታሪክ ሰው ተክለጻዲቅ መኩሪያ ደግሞ ‹‹ኦሮሞዎች በ16ኛው ክፍለ-ዘመን በአፄ ልብነ-ድንግል ዘመነ-መንግሥት ፈልሰው መጡ›› የሚለውን መከራከሪያ ሃሳብ በማስረጃ ውድቅ ያደርጉታል። ከአውስትራሊያም ይምጡ ከእስያ፣ በሞዛምቢክ በኩል ይምጡ በማደጋስካር፣ በታንጋኒካ/ታንዛኒያም/ ይሁን በኬንያ፣ ብቻ ያ ወቅት /16ኛው ክፍለ-ዘመን/ ኦሮሞዎች ወደ ኢትዮጵያ የገቡበት ሳይሆን ከደቡብ ኢትዮጵያ ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ፣ ወደ ማህል ሸዋ፣ ወደ ዳሞት፣ ወደ ጎጃምና በጌምድር የተንቀሳቀሱበት መሆኑን ያረጋግጣሉ። ቆየት ብለውም ‹‹ሳሎ›› የተባለ አንድ የኦሮሞዎች መሪ መና-እስራኤል ከተባለችና የንጉሣውያን ወገን ከሆነች ሴት ወይዘሮ ከረዩ፣ ሜጫ፣ ቱለማ፣ ወሎ፣ እልክ፣ ዱሬቲ እና አያንቱ የተባሉ ስድስት ልጆችን ወልዶ በየስማቸው ነገዶች ተመስርተዋል ይሉናል።(7)

ምንም እንኳዋን ተክለ ጻዲቅ መኩሪያ ምንጫቸውን ባይነግሩንም የሳሎ እና የመና-እስራኤል ታሪክ ምንጭ ከአለቃ አጽመ-ጊዮርጊስ ውጪ ሌላ ሊሆን አይችልም።

ከለንደን ዩኒቨርስቲ በምጣኔ ሀብት ምሩቅ የሆኑት እና በአፄ ኃይለሥላሴ ካቢኔ ውስጥ ሚኒስትር ሆነው ለበርካታ ዓመታት ያገለገሉት ይልማ ደሬሳ ደግሞ የኦሮሞን ከየት መጣነት ለመግለጽ የኦሮሞን እና የሶማሊን የቃል ትውፊት እና ሥነ-ቃል መሰረት ያደርጋሉ። ለአባ ባሕርይ፣ ለአለቃ አጽመ-ጊዮርጊስ እና ለልጅ ተድላ ኃይሉ ሥራዎችም እውቅና ይሰጣሉ። ይልማ ደሬሳ እንደሚሉት ኦሮሞ ወደ ኢትዮጵያ ከመፍለሱ በፊት በአስረኛው ክፍለ-ዘመን በአፍሪቃ ቀንድ ዛሬ ሶማሊያ ተብሎ በሚጠራው አገር ይኖር ነበር። (8)

መሐመድ ሃሰንም አባ ባሕርይን፣ አንቶይኔ ዲ. አባዴን፣ እ.ቸሩሊንን፣ አይ.ኤም.ሌዊስን፣ ኤ. ሃበርላንድን እና ዩ. ብራውካምፐርን ዋቢ በማድረግ ጀርመናዊው ኤ. ሃበርላንድ “የኦሮሞ ዝርያዎች በቀዝቃዛው የባሌ ተራራዎች ላይ ኖረዋል” ባለው ሀሳብ ይስማማል።(9)

ጌታቸው ኃይሌም አይከ ሀበርላንድን፤ አለቃ አፅመጊዮርጊስን፥ አለቃ ታዬን እና አለቃ ተክለእየሱስን ጠቅሶ ኦሮምኛ ከሌሎቹ የኢትዮጵያ የኩሽ ቋንቋዎች፥ ለምሳሌ ከሶማልኛና ከቅማንት ጋር ያለውን አንድነትና ትስስር መሰረት በማድረግ ወደ ኢትዮጵያ የፈለሱት በቅርቡ ነው ለማለት እንደሚያስቸግር ይገልፃል። ቀጥሎም፥ ከመሃል ኢትዮጵያ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ወርደው ከማእከሉ መንግሥት ጋር ለዘመናት ተቆራርጠው፥ ባህር-ገሞ ከሚባል ስፍራ ቆይተው፥ እንደገና ከዛው ቦታ ተነስተው፥ ወደ መሃል ኢትዮያ የተመሙ ሊሆኑ ይችላሉ ይላል። ሆኖም እዛው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው የተፈጠሩት ብሎ የተፈጠሩበትን ስፍራ በትክክል ጠቁሞ በአፉ ሙሉ አይናገርም።(10)

ቦኒ ኬ ሆሎኮምብ የተባለች ፈረንጅ እና ሲሳይ ኢብሳ የተባለ አሮሞ፥ ሁለቱም ኦሮምያ ቅኝ የተገዛች መሆንዋን ለማሳመን ደፋ ቀና የሚሉ ሰዎች ደግሞ ኢትዮጵያ የኦሮሞዎች ሃገር እንደሆነች በፍፁም አልከተቡም። እነሱ የሚሉት እንደሚከተለው ነው፦

*"የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ አብዛኛው ህዝብ የኦሮሞው ነበር። አገራቸውም ውሃ በጣም የጠገቡ፥ እስከ ማእከላዊ እና ደቡባዊ የአፍሪካ ቀንድ የሚደርስ መካከለኛ፥ እንዲሁም ከፍተኛ እና ዝቅተኛ መሬቶችን የሚያጠቃልል ነበር።"* (11)

እንደሙዋቹ ባለታሪክ እንደ ሃሮልድ ማርከስ አስተያየት የኦሮሞዎች ምንጭ በቀጥታ ኢትዮጵያ ውስጥ ሳይሆን ኬንያን በሚያዋስነው የኢትዮጵያ ዳር ድንበር ነበር። የእሱም አስተያየት መላ-ምት ነው። እንደዚህ ይላል፦

*"ኦሮሞዎች፥ አነዛ በኩሽ ቋንቋዋ ይናገሩ የነበሩት ከብት-አርቢዎች፥ ምንጩ-ሃገራቸው ሰሜን-ምዕራብ ቦረና ነበር። ከነሱ ቀደም ብለው የ አፋር-ሳሆ እና የሶማሌ ወንድሞቻቸው በስተ ሰሜን-ምስራቅ፥ በህንድ ውቅያኖስ ወደቦች፥ በኤደን ሰላጤ እና በቀይ ባህር አካባቢ ሰፍረው ነበር። ምናልባት በ 13ኛው ምዕተ-ዐመታት መጨረሻ ላይ ጥቂቶች ኦሮሞዎች በከፍታ ላይ የነበሩትን ሜዳዎች ይዘው ሊሆን ይችላል። ሆኖም ወደ ኢትዮጵያ እንዳይዘልቁ ዳር ድንበሩን ይጠብቁ በነበሩት ሰለሞናዊ ወታደሮች ተገዝተው ነበር። ማዕከላዊ መንግሥት ከሙስሊም ኃይሎች ጋር ጦርነቶች ገጥመው እነዚህ ኬላዎች በተደፈሩ ጊዜ እነዚህ ኦሮሞዎች ሰርገው ወደ ውስጥ ለመግባት ችለዋል። ወቅቱም አፄ ልብነድንግል በኢትዮጵያ ጠረፎች ላይ መንግሥት ብጤ ለማቋቋቋም የሚጥሩበት ነበር።"* (12)





እስካሁን ስለ ኦሮሞ አመጣጥ የተሰነዘሩ የተለያዩ አስተያየቶችን ቃኘን። ስለ አማራ አመጣጥ የተጻፈውም እንዲሁ አጠራጣሪ ነው። ተክለ ጻዲቅ መኩሪያ እና አለቃ አጽመ-ጊዮርጊስ እርስ በርሳቸው ይቃረናሉ። ተክለጻዲቅ መኩሪያ አማራ ከደቡብ አረቢያ ቀይ ባሕርን ተሻግሮ መጣና በኢትዮጵያ ሰፈረ ብለው ይከራከራሉ።(13)

አለቃ አጽመ-ጊዮርጊስ ደግሞ አማሮች የኢትዮጵያ ነባር ነዋሪዎች መሆናቸውን ያረጋግጣሉ። አለቃ እንደሚሉት አማሮች አንድ ነገድ ብቻ አይደሉም። ከተለያዩ ነገዶች ተውጣጥተው (በዛጉዌ ስርወ-መንግሥት ወቅት) በላስታ ላሊበላ የተሰባሰቡ የአስፈሪ ወታደሮች ስብስብ ናቸው። በዚህ መሰረት አማሮች የታዩት በአሥረኛው ክፍለ-ዘመን ገደማ ነው ማለት ነው። አለቃ ያሉትን ቃል በቃል ብንጠቅስ፤ *‹‹አማሮች ከየትም አልመጡም። ከተለያዩ ነገዶች የተሰባሰቡና ከላስታ ጦር ሠራዊት የተራረፉ ሃይለኞችና ብልሆች፤ ነገርግን ያልተማሩና ጨካኝ የሆኑ ወታደሮች ናቸው››(14)*

ባሕሩ ታፍላ እንደሚሉት ደግሞ የአማራ ጥንተ-ስር አይታወቅም። *‹‹ትክክለኛው የአማራ ጥንተ-ስር አይታወቅም፤ ሆኖም ቢያንስ በፖለቲካ የበላይ ከሆኑበት እና በአጎራባቾቻቸው ላይ የቋንቋና የባሕል ተጽእኖ ማሳረፍ ከጀመሩበት ከ13ኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ ሳይንት፣ ዋድላ፣ ደላንታ፣ መቄት፣ ሳዳሆ፣ ላስታ በከፊል፣ ጋኝ እና ሸዋ በከፊል መኖሪያ ቦታዎቻቸው መሆናቸው ግልጽ ነው››* ሲሉ ይደመድማሉ። (15)

ኦሮሞው እና አማራው ከሞላ ጎደል በሁሉም ምሁራን ኩሻዊ እና ሴማዊ ተብለው የተከፈሉ ተቃራኒ ዝርያዎች ተደርገው ይቆጠራሉ። በሌላ አባባል ኦሮሞው ኩሻዊ፣ አማራው ደግሞ ሴማዊ ተደርጎ ይታያል። እኔ እስከማውቀው ድረስ ከአንድ ዘር የመጡ ስለሆኑ ሁለቱም ኩሻውያን ናቸው። ለሁለቱም ምንጫቸው ሌላ ሳይሆን ጎጃም ነው። ኢትዮጵያ ናት። ምንም እንኳዋን ጥቂቶቹ

በወታደራዊ አገልግሎት፤ የተሻለ መሬት በመፈለግ፤ በጀብዱና በመሳሰሉት ምክንያቶች ኢትዮጵያን እየተዉ ወደ ምሥራቅ አፍሪቃ፣ ማዳጋስካር፣ አረቢያ፣ ኑቢያ፣ ግብጽ፣ ሊቢያ፣ ናይጀሪያ፣ ማሊ፣ ማውሪታኒያ እና አልፎም ወደ እስያ በተለያዩ ጊዜያት እየሄዱ ቢመጡም፤ አንዳንዶቹም በየሄዱበት ቢቀሩም ኦሮሞና አማራ ከ3500 ዓመታት በፊት ጀምሮ በጎጃም እና በሌሎችም የኢትዮጵያ ግዛቶች አብረው አንድ ላይ ኖረዋል። ይህን በቦታው እዘረዝረዋለሁ።

ኒውዮርክ ታይምስ፣ እንደ አውሮጳ አቆጣጠር ቅዳሜ ጥቅምት 21 ቀን 2006 ዓ.ም እንደሚከተለው ጽፏል፡-

*‹‹ባግዳድ፣ ጥቅምት 20- ከሺኣይት ፀሐፊ ከማከታዳ ኣል-ሳዳር ጋር ግንኙነት ያላቸው በመቶዎች የሚቆጠሩ ሚሊሻዎች በደቡባዊ ምሥራቅዋ አማራ ከተማ አርብ ዕለት ያካባቢውን ፖሊስ ጣቢያ እና የሺኣይት ሚሊሺያ ተቃዋሚ የሆኑትን አጥቅተው ፖሊስ ጣቢያውን ደምስሰዋል። አካባቢውን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥረዋል፤ ሰማዩን በጪስ የሸፈኑ ቦንቦችንም አፈንድተዋል››*(16)

እዚህ ላይ ‹‹አማራ›› የሚል ቃል እንበብኩ? ብለው ግር ይሰኙ ይሆናል። በትክክል አንብበዋል። ኢራቅ ውስጥ "አማራ" የሚል ከተማ ከየት መጣ? በቦታው እብራራዋለሁ። ሦስት ሺ አመትና ከዚያም በላይ የገዙ ኢትዮጵያውያን ንጉሦችንና ንግሥቲቶችን ዝርዝር ስንመለከት የአማርኛ ስሞች ያጋጥሙናል። ያ ማለት ታዲያ ንጉሦቹና ንግሥቲቶቹ የግዴታ አማሮች ነበሩ ማለት አይደለም። ወይም ደግሞ የአማራን ሥርወ-መንግሥት ይወክላሉ ማለትም አይደለም። የአማራ ሥርወ-መንግሥት የሚባል ነገርም አልነበረም። በርግጥ እነዚህ ነገሥታት መጀመሪያ በኢትዮጵያ ቀጥሎ ደግሞ በሰለሞናዊው ሥርወ-መንግሥታት ስር ገዝተዋል። ቀዳማዊ ምኒልክ ከአይሁድ ዘመዶቹ ጋር ሆኖ ‹‹*ኣግአዚ*›› ብሎ የጠራውን የራሱን መንግሥት ከመሰረተ በሁዋላ ሰለሞናዊ ሥስርወ-መንግሥት ወደ ኢትዮጵያ ተሻግሮአል። ለምሳሌ ምኒልክ የሚለው የአማራ ስም ቢሆንም ሰውየው ግን አማራ እንዳልሆነ በደንብ እናውቃለን። ዘግዱር(ዝግ-ዱር፣ ጥቅጥቅ ያለ ደን) እና ዘዋሬ-ንብረት(ተንቀሳቃሽ ንብረት) ለተባሉት ዝርያዎቹም ሁኔታው ተመሳሳይ ነው። ከ3ሺ እምስት መቶ ዓመት በፊትና በሁዋላም አማራና አማርኛ መኖራቸውን የሚያረጋግጡ ጥቂት የአማራ ስም





ያላቸው የኢትዮጵያ ነገሥታት ቀጥሎ ቀርበዋል። አማራና አማርኛ ከሶስት ሺ አምስት መቶ እመት በላይ መኖራቸውን ጥቅሱ ያረጋግጣል። ከሞረሽ ጀምረን እስከ ላሊበላ ድረስ ብንጠቅስ የመጀመሪያው ሞረሽ ከ3500 ዓመት በፊት ኢትዮጵያን የገዛ ሲሆን የመጨረሻው ላሊበላ ደግሞ ከ826 ዓመት በፊት የኢትዮጵያ ንጉሠ-ነገሥት የነበረ ነው።

ሞረሽ...................በሌሊት የሚያስፈራ ስምን የሚተካ

ሰንደቅ ዓልማ...... ባንዲራ፣ ግብ

ዓለም ሰገድ..........ድፍን ዓለም የሚሰግድለት ሰው

አሜን..................ይሁን፣ ይፈጸም

መረብሳባ...............መረብ-ሳቢ፣ መረብ የሚጎትት ዓሳ አስጋሪ

አሞር፣ አማራ........እሞራ፣ ጆፌ አሞራ

ኩርፋ...................ዥጉርጉር እባብ

ሰርፌ፣ ዘርፌ.........(ዘርፍ፣ የግርጌ ጌጥ)

ምኒልክ..................(ምን ይልክ  ይሆን)

ዘግዱር..................ጥቅጥቅ ያለ ደን፣ የማያስልፍ ጫካ፣ዝግ-ዱር

ባለ-ፀሀይ................የኮከብ ምልክቱ ፀሀይ የሆነ

ወረደ-ፀሃይ.............ነደ-ፀሃይ፣ የወረደ ፀሀይ፣ በጣም ሞቃት

ወጪጥ፣ እውጥ........ኪኒን፣ የሚበሉ ትናንሽ ፍሬዎች

ዘዋሬ-ንብረት............ተንቀሳቃሽ ንብረት

ሰይፈ.....................የኔ  ሰይፍ

ራስ-ዳሽ..................ራስ እዳሽ

ገርላሞት……………..ሞትን የምትገረስስ፣ ሞትን ድል የምታደርግ

ቢልለቢላ…………………ቢልቢላ፣ ስለተናገርኩ ተናገረች፣ ትንሽ ደወል፣ ቃጭል እንደማለት

አልነጋሽ……………..ንጉሥ

አርማሕ……………ምልክትህ

ግርማ አስፈሪ………ግርማው የሚያስፈራ፣ ግርማ ሞገስ ያለው

አል ባሕር ነጋሽ……የባሕር ጠረፍ ንጉስ

ድግ…………………መቅነት

ጉም…………………ዳመና

አስጉምጉም…………በዳመና ሸፍነው

በካሣ…………………በበደል፣ በድካም ዋጋ፣ በማካካሻ

ልትም………………የተጋጨ

ተላተም……………ተጋጭ

አይዙር……………ፊቱን አይመልስ፣ አይሸሽ

ውድም አስፈሪ……..በጦር ሜዳ ጠላቱን የሚያስፈራ፣ ወገኑን የሚያነቃቃ

ነጋሽ ዛሬ…………ዛሬ የሚገዛ ንጉሥ

መራ ተክለ-ሃይማኖት…የሃይማኖት መሥራች አለቃ

መሪመራሪ ድላድ……ያንድ ድል መሪ

ላሲበላ………………ማር የሚበላ (17)፡፡





በዚህ መሰረት በርካታ ነገሥታት የአማርኛ ስሞች ያላቸው በመሆኑ አማርኛ እና አማራ እንደ ቋንቋ እና እንደ ሕዝብ ከ3500 ዓመት በፊት ጀምሮ ኖረዋል ማለት ነው፡፡

ኦሮሞውን በተመለከተ ባመዛኙ ኦሮሞው መደባይ፥ ጂማ እና መንዲ ከተባሉ ነገድ መምጣቱንና የመደባይ ሁለት ወንድሞችም ጂማና መንዲ መሆናቸውን ዘረ-ሃረጋቸው ያረጋግጣል፡፡ ከነዚህ ሶስት ወንድማማቾች መሀል መደባይ የታላላቆቹን አባቶቻቸውን የእነ ኢትዮጵን እና የነ ደሴትን ቅስናና የጥበብ መፃህፍት በመውረሳቸው ጠቢባን እና ካህናት ለመሆን በቅተዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ በቤንሻንጉል-ጉምዝ ክልል አሶሳ ወይም መተከል አካባቢ እና በአማራ ክልል ጎጃም ዞን ወንበራ ወይም ወንበርማ በተባለ ቦታ በዚህ ‹‹መደባይ›› በሚለው ስም የሚጠራ እና ኦሮምኛ የሚናገር ነገድ አለ፡፡ በብልሕነቱና የባሕል መድሃኒት ቀማሚነቱ ይታወቃል፡፡ የኢትዮጵና የደሴት (ደሸት) ዘር በመሆኑ ነው፡፡

አንደ እውነቱ ከሆነ በሁለቱም በኦሮሞም በአማራም ይነገር በነበረውና ‹‹ሱባ›› በተባለው ቋንቋ ‹‹መደባይ›› ማለት ‹‹ፈላስፋ፣ መራቂ፣ (የሚመርቅ) እና ቄስ›› ማለት ነው፡፡ ሦስቱ ሰዎች “ማጂ” የተባለና ለአማራ እና ለጃማ ጎሣዎች አባት የሆነ ወንድም ነበራቸው፡፡ ማጂ ማለት “ብልሕ” ማለት ነው፡፡ ማጂዎች ለህፃኑ ኢየሱስ ስጦታ ለማበርከት ከምሥራቅ ኢትዮጵያ ወደ ቤተልሄም ከተጓዙ 12ቱ ብልሖች መካከል ናቸው፡፡ ‹‹ማጂክ›› የሚለው ቃል የመጣው ከብልሕነታቸው የተነሳ ከነሱ ስም ይመስለኛል፡፡

በእርግጥ መደባይ፣ ጂማ፣ ማጂ እና መንዲ ወንድማማቾች ናቸው፡፡ አባታቸው ደሸት ወይም ደሴት የነቢይት ልጅና ራሱም ነቢይ፣ ፈላስፋና ንጉሥ የነበረ ሲሆን ጎጃም በጣና ሐይቅ አካባቢ ይኖር ነበር፡፡ ጣና ሐይቅንም ያስተዳድር ነበር፡፡ ደሴት የሚለው ስያሜ የተወለደው ከሱ/ከመሪው/ መጠሪያ ነው፡፡ ከ3500 ዓመት በፊት ነው የኖረው፡፡ አምን ልጆቹ እያንዳንዳቸው ኦሮሞንና አማራን ጨምሮ የበርካታ ነገዶች አባቶች ሆነዋል፡፡ ይህን ነጥብ ወደፊት አብራራዋለሁ፡፡ መደባይ የተባለ አገር በአክሱም ከተማ እና በመረብ ወንዝ መካከል ዛሬ ድረስ አለ፡፡ መደባይ ታቦር እና መደባይ ወለል

ተብሎ በሁለት ተከፍሏል። ይህ ‹‹መደባይ›› የተባለ ነገድ ከ3000 ዓመት በፊት መኖሩ በአለቃ አጽመ-ጊዮርጊስም ተረጋግጧል።

*‹‹የመጀመሪያው ጨዋ (ጨዋ ማለት ወታደር ማለት ነው) በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን የነበረው መደባይ ነው። እነሱም በትግሬ፣ በስሜን፣ በፀለምት እና በወገራ ለፍረው የነበሩ ወታደሮች ናቸው። ከሱ (ከቀዳማዊ ምኒልክ) በሁዋላ የተነሱ ነገሥታትም እንዲሁ አድርገዋል። በሁዋላ፣ በ1130 ወይም በ1150 ዓ.ም በንጉሥ ላሊበላ ዘመን "አማራ" የተባሉ ወታደሮች በዋድላ፣ በበጌምድር፣ በሳይንት እና በወለጋ "ጨዋ"/መደበኛ የመንግሥት ጦር/ ሆኑ። በባላገሩ ላይ ተሰሪነት ገቡበት››*(18) ይላሉ አለቃ አፅመ-ጊዮርጊስ።

ከላይ በቀረበው ጥቅስ አለቃ አጽመ-ጊዮርጊስ ሦስት እውነታዎችን ነግረውናል፡-

ሀ. *መደባይ የተባለ ነገድ ከሦስት ሺ ዓመት በፊት ኢትዮጵያ* ውስጥ ይኖር ነበር።

ለ. ይህ *መደባይ የተባለው ነገድ ኦሮሞ ሲሆን የመጀመሪያው* "ጨዋ" *ማለትም መደበኛ የ*ጦር *ሠራዊት* ነበር።

ሐ. ሁለተኞቹ ጨዋዎች /*መደበኛ ወታደሮች*/ አማሮች ነበሩ፤ ይህም ከ2000 ዓመት በሁዋላ በንጉሥ ላሊበላ ዘመን ነው።

ላሊበላ በ11ኛው ክፍለ-ዘመን ሥልጣን ላይ ሲወጣ ባመዛኙ በአማሮች መደገፉ እውነት ቢሆንም ከዚያ በፊት አማራው ጨዋ /መደበኛ ወታደር/ አልነበረም ማለት አይደለም። የቀዳማዊ ምኒልክ የልጅ ልጅ ታላቁ አክሱማይ ከ2850 ዓመት በፊት ገና በ6 ወይም በ7 ዓመት እድሜው በግብጽ ላይ ‹‹ፈርኦን›› ተብሎ ሲነግስ አማሮች ነበሩ ዙፋኑን የጠበቁለት። ይህን ቆየት ብዬ አብራራለሁ። የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከሆነ በኋላ ‹‹ሪብላ›› የተባለች ሴት ልጁን ለሜሶጶታሚያ ንጉሥ ለናቡከደነጾር ሚስት ትሆነው ዘንድ በበርካታ የአማራ ወታደሮች አሳጅቦ (እና የመንግስት አማካሪዎችንና ጠቢባንን ጨምሮ) ወደ ሜሶጶታሚያ ላከለት። በዚህ መሰረት ነበር ዝቅ ብለው የሚያገኙዋት ‹‹አማራ›› የተሰኘችው ከተማ በአሁኗ በኢራቅ የተመሰረተችው።





*ሚያዚያ* 5 *ቀን* 505 *ዓ.ም የተወለደው ቅዱስ ያሬድ (የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ዜማ ደራሲ ማህሌታዊ ያሬድ)* በቅድመ-አያቱ ኦሮሞ ከሆነች *መደባይ ይወለዳል።* እንደ አውነቱ ከሆነ በአባቱ በኩል የንጉሣዊ ቤተሰብ አባል የሆነ አንድ ዘመዱም *መደባይ*/ኦሮሞ ነው። አክሱም አጠገብ *መደባይ* የተባለ ቦታ ተገኝቷል። *ያሬድ* አክሱምን ከለቀቀ በኋላ እናቱ ወደምትኖርበት ወደዚህ *መደባይ* ወደ ተባለው ቦታ ነው የሄደው።(19)

በዚያን ወቅት ከንጉሠ-ነገሥት አክሱማይት ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ ነገሥታት ኢትዮጵያውያን ዘመዶቻቸው የሆኑትን ልዕልቶችን ‹‹ሕንደኬ›› የሚል የማዕረግ ስም እየሰጡ በግብፅ፣ በሊቢያ እና በኑብያ ንግሥቶች እያደረጉ የማንገሥ ልማድ ነበራቸው። እነዚህ ተሸዋሚ ንግሥቶች ከነገሡ በሁዋላም ያንጋሾቻቸው ንጉሣውያን ቤተሰብ አባላት ነበሩ። ከ2500 *ዓመታት በፊት መርዌን እንድትገዛ* በአፄ ፈንታሌ ነግሣ የነበረችው ሦስተኛዋ ሴት ፋሲላ እኖኒ የምትባል *መደባይ* ነበረች። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ኦሮሞ ነበረች ማለት ነው።(20)

*ታሪከ-ነገሥት* እንደሚለው ቀዳማዊ አፄ ዮሃንስ (ከ1660-1674 የገዙት) ከንግሥት ሰብለ-ወንጌል (*የመደባይ* ነገድ ከሆነችው) አፄ ኢያሱን ወለዱ።(21)

በትግራይ ክልል ውስጥ *መደባይ* ዛና የተባለ አካባቢ አለ። ትግራይ ካሉዋት 36 ወረዳዎች አንዱ ነው። ትግራይ ከጎጃም በስተሰሜን እንደመሆንዋ የተወለኑ *መደባዮች* (ኦሮሞዎች) ከዋናው *መኖሪያቸው* ከጎጃም ትንሽ ከፍ ብለው አሁን ትግራይ በሚባለው ቦታ ሰፍረዋል ማለት ነው። ቆይተውም ከዚያ አልፈው ወደ ደቡብም ሄደው ዛሬ ወለጋ፣ ሊሙ እና እናሪያ በሚባሉት ቦታዎችም ኖረዋል። በትግራይ ውስጥ ከሌሎች ነገዶች ጋር ራሱን የቀላቀለው *መደባይ* (ኦሮሞ) ልክ የራያ ኦሮሞ ኦሮምኛን ትቶ ትግርኛ እንደሚናገረው ባሁኑ ወቅት ትግርኛ ተናጋሪ ሆኗል።

አማራውን በተመለከተም ከቀዳማዊ ምኒልክ መወለድ በፊት ጀምሮ ለመኖሩ ሌላው ማስረጃ ቀዳማዊ ምኒልክ ከንግሥት ሳባ እና ከንጉሥ ሰለሞን ከሦስት ሺ ዓመት በፊት ሲወለድ አማሮች "ምኒልክ"

ብለው ስም ማውጣታቸው ነው። ፍቺውም "አባትህ ስለሞን ቢያይህ ምን ይልክ ይሆን?" ማለት ነው። አማሮች በቋንቋዋቸው ስም ስማውጣት በቅድሚያ ራሳቸው እንደ ሕዝብ መኖር አሰባቸው። ሁሰቱም፣ አማራም ኦሮሞም ከሶስት ሺ ዓመት በላይ በኢትዮጵያ ውስጥ ኖረዋል የምልበት አንድ ተጨማሪ ምክንያት ይህ ነው።

የመደባይ፣ ጂማ እና መንዲ ዝርያዎች በንጉሠ-ነገሥት አፄ (ኤሰያ-ኤል) ስመ-መንግሥቱ ‹‹ሰንደቅ-ዓላማ›› በነበረው ዘመን ሰምንት ንጉሦች ሆነው ነበር። በዘጠነኛው ክፍለ-ዘመን አስቴር ትባል በነበረችው በፈላሻዋ ዮዲት-ጉዲት ወረራ ምክንያት ከአክሱም ወደ ኑቢያ የተሰደደው የቤተመንግሥቱ ታሪክ ፀሓፊ ‹‹አክሱማይ ሊራክ›› በተወልን መረጃ ላይ ስምንት የኢትዮጵያ ክልሎችን ከ3200 ዓመት በፊት የገዙ ሰምንት ንጉሦችን ስም ዝርዝር እናገኛለን። እነዚህ የሶስት ወንድማማች ልጆች በጊዜ ሂደት ውስጥ ራሳቸውን አባዝተው የየራሳቸውን ነገድ መሰርተዋል። ሰማቸውን፣ የገዙትን ክልል፣ ወንዛቸውንና የነገዳቸውን ስም ቀጥሎ እጠቅሳለሁ።(22)

| የንጉሱ ስም | ክልል | ወንዝ | ነገድ |
|---|---|---|---|
| ዳሞት | ሞጣ | ግዮን | መደባይ፣ማጂ፣ጋፋት |
| ሀዲያ | ኤውላት | ዋቢ(ኦጋዴን፣ሶማሊያ) | ጂሬ፣ዋጂራ፣ቦነጋ |
| ጎጃም | ደሼት(ደሴት) | ግዮን | መንዲ፣ዌንጌ |
| ኮንሺ | ሰገል | ነገሌ | ቦረና፣ቱሰማ፣አባታሊት |
| ሰኑካ | አዝ | ገናሌ | ብርቱማ፣ጋሊ፣ጂሎ |
| ጭላሎ | ሃጌ | አዋሽ | ኢሳ፣ሓሼን፣ሲዳማ |
| መጋል | ሞራ | ጊቤ | ሞያ፣ሆሮ-ወላቦ፣ቦረን፣ኢቱ |
| ጋውል | ኤዜር | ጂባ | ወረማያ |





ከአምስት መቶ ሃምሳ ዓመት በሁዋላ በአክሱማይ ዘመነ-መንግሥት ይሄውም ከ2850 ዓመት በፊት ከላይ የተጠቀሱት ነገዶች ራሳቸውን አባዙ። የመደባይ ነገድ ዝቅ ብዬ በምገልፀው ምክንያት ራሱን ኦሮሞ አያለ መጥራት ጀመረ። አሁን በንጉሠ-ነገሥት አክሱማይ ዘመነ-መንግሥት ተመዝግበው የነበሩትን ነገዶች እንመልከት፡-

| የነገድ ስም | የክልሉ አጠራር | ክልል | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| ኦሮሞ | እናርያ | ማያ፣ወረማያ ማያ | |
| ጋሊ፣ገላ | ውቂሮ | ውቂሮዪያ | ከጊዜ በሁዋላ ጋላ ተባሉ። በኦሮሞና በጋላ ነገዶች መካከል ልዩነት መኖሩን ልብ ይሉዋል። |
| ደራስ | ሆር-ወላቦ | አዋላቢያ | |
| ቦረን | ኪንዶ፣ሀዲያ | ሀደያ | |
| በርቱማ | ጥሞጋ | ሞጋብያ | |
| ከረዩ | መረዋ | መረዋኒያ | |
| ኢቱ | ሞራ | ሞራና | |
| አከቹ | ወረን | ወረያ | |
| ሊበን፣ጃዊ | ጎጃም | ደሼት፣ደሴት | (የኦሮሞ እና የአማራ ቀደምት አባት) |
| ሜጫ | ለ'ማ | ሱማሊያ | |
| ሰል፣ሰላሌ | ገነት፣ወሌ | ወልዲያ | |
| ሰዳሞራ | አሙሩ | ሺቦቃ፣ጂሬ፣ዋጂራ | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ጆሌ | ጨፋ | ገነቲያ፣ወረን | |
| አዳል፣አዛር | ላዶር | አንፋሪያ፣ አባታላት | |
| ሀሼን | ሀሼንጌ | ሀሼን፣ ደርዲ | |
| ማያ | ገበታን | ዝዋይ፣ ሱቂ | |
| ሰደቻ | ቆቦ | ራያ፣ ማጂ | |
| ጼራ፣አርሆ | ጉማይ | ግምያ፣ መንዲ | |
| ቦፋት | ቶቤ | ቦባሳ፣ ማሲያ፣ | ሞምባሳ፣መሳይ፣በሁዋላ ኬንያ |
| ከምባታ | ወላሞ | ቦ፣ ኪኩያ | በሁዋላ ኬንያ |
| ጋፋት | ከፋ | ከፋኢ፣ሲሲ | |
| እማሮ | ኩሌ | መንድያ፣ቡዱ፣ሚድን ስከያ | |
| ጂሬ | ዋጂራት | …………… | |

ከላይ የተዘረዘሩት ሁሉም ነገዶች ከዛሬው ኦሮሞ ጋር ይዛመዳሉ፡ አብዛኞቹ አለካሁን ድረስ በኢትዮጵያ ይኖራሉ። ተወላጆቻቸው ሶማሊ ኪኩዩ እና ማሳይ ነገዶች እንደ ቀደም ተከተላቸው በሶማሊያ አና በኬንያ ለፍረዋል። የኬንያዎቹ ማሳዮችማ ቁርጥ ኦሮሞዎችን ናቸው፡ የኦሮሞን ባሕል አሁን ድረስ በሚያንፀባርቁበት በምርቃታቸው ይታወቃሉ። የምርቃቱ ምንጭም የጥንት አባታቸው (የኢትዮጵ አባት መልከጼዴቅ ነው። መልከጼዴቅ ቀደም ሲል እንዳልኩት የንጉሦች ንጉሥ እና ከፍተኛው የሳሌም (የኢየሩሳሌም) ካሕን የነበረ ሲሆን አብርሃም በሶዶምና ጎሞራ ዙሪያ የነበሩትን ነገሥስታት ድል አድር ሲመለስ ባገኘው ጊዜ ዐስራት አግብቶለት የባረከውና የመረቀው ነው።





# ኦሮሞና አማራ በዘር አወራረድ

ከላይ እንደጠቀስኩት ኦሮሞና አማራ በዘር አወራረድ ሥረ-መሠረታቸው አንድ ነው። አንባብያን ቢያምኑትም ባያምኑትም የዘር ምንጫቸው የሚጀምረው ከኢትዮጵያ ውጪ ወይም እዛው ኢትዮጵያ ውስጥ ሲሆን ይኸውም ከአምስት ሺ አምስት መቶ ዓመት በላይ ዘመን አለው። መጀመሪያ የዘር አመጣጣቸውን እገልጽና ለጥቂ ዝምድናቸውን በዝርዝር አስረዳለሁ። .

የዘር አወራረዳቸው ከኖህ ልጅ ከሀም/ካም/ እና ከጥፋት ዉሀ በኋላ ከበለጸገው ከልጁ ከኩሽ ይጀምራል። የኖኅ መርከብ ጎጃም ውስጥ ከሚገኙ አራት ተራራዎች ባንዱ ላይ እንዳረፈች እገምታለሁ።ይህን የሚጠቁሙ መረጃዎች አሉና። እንደዛ ከሆነ ደግሞ እዛው ኢትዮጵያ ነው ማለት ነው የነበሩት። ይህ ነጥብ የመከራከሪያ ርዓሰ-ጉዳይ ሊሆን ስለሚችል እዚህ አልሟገትበትም። ኦሮሞዎች ኩሻውያን (የኩሽ ዘርያዎች) መሆናቸውን የሚያስምሩበት ለዚህ ሳይሆን አይቀርም። ኩሽ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል አይደለም የምንል ለዎች እንኩዋ የታሪክ ማስረጃነቱን ብንቀበልም ባንቀበልም ኩሽን ይጠቅሰዋል። የታሪክ ለዎች ይህን ቃል መጀመሪያ ያገኙት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው። እንደሚከተለው ይነበባል፡-

ካም ኩሽን ወለደ። ኩሽ ሳባን (ሴት ሳይሆን ወንድ ነው) ወለደ። ሳባ ኑባን ወለደ። ኑባ ጋናን ወለደ። ጋና ኢታናን ወለደ። ኢታና ናምሩድን ወለደ (ናምሩድ የባብዔልን ማማ የለራ ነው)። ናምሩድ አዳማን ወለደ (በኦሮምያ ክልል የምትገኘው የዛሬዋ ናዝሬት-አዳማ ከተማ መጠሪዋን ያገኘችው ከዚህ ነው)። አዳማ ራፌልብን ወለደ። ራፌልብ ቀንአን ወለደ። ቀንአ ጌራን (ከፍተኛውን ካሕንና የሳሌምን/የኢየሩሳልምን/ ንጉሥ መልከጼዴቅን) ወለደ። ጌራ ወይም መልከጼዴቅ፥ በጣና ሐይቅና በግዮን ወንዝ አካባቢ ከ 4000 ዓመት በፊት የኖረውን ኢትዮጵ ተብሎ እንደገና የተሰየመውንና በኢትዮጵ ማለትም በቢጫ ወርቅ በተሞላው ቦታ ለፋሪውን ኤት-ኤልን ወለደ። ኢትዮጵ ማለት "ለእገዚአብሔር የቢጫ ወርቅ ሥጦታ" ማለት

ነው፡፡(24 ) "ኢትዮጵ" በሚሰው መጨረሻ ላይ "ያ" ን ስናክልበት 'ኢትዮጵያ'" የሚሰውን ቃል እናገኛለን፤ ይህም እስካሁን ኢትዮጵና ዝርያዎቹ የሚኖሩባት አገር መጠሪያ ነው፡፡ የኢትዮጵን ዝርያዎች ጥቂት ገጾች ዝቅ ብዬ እዘረዝራለሁ፡፡

"ኢትዮጵያ" የሚሰውን ማንነታችንን በተመለከተ "መጠሪያችንን ያወጡልን ግሪኮች ናቸው፤ ኢትዮጵያ ማለትም ‹ፊቱ በፀሐይ የተቃጠለ ማለት ነው› የሚሰውን መንደርደሪያ ተቀብለን ስንኖር ተሳስተን ነበር፡፡ ጨርሶ ከእውነቱ የራቀ ነው፡፡ ግሪኮች ወደ ስልጣኔና ፖለቲካው መድረክ የመጡት ታላቁ ተብየው አሌክሳንደር በ300 ዓመተ-ዓለም ገደማ ከፊል ግብጽን ወርሮ በርካታ ቶኖች የሚመዝኑ ብርቅዬ መጻሕፍትን ዘርፎ ከወሰደ በሁዋላ ነው፡፡ መጻሕፍቱ በፍልስፍና፣ ሕክምና፣ ሒሳብ፣ ጂኦሜትሪ፣ ጂኦግራፊ፣ አስትሮኖሚ፣ አስትሮሎጂ፣ ሃይማኖት ወ.ዘ.ተ. ላይ የተጻፉ ሲሆኑ ጸሓፊዎቹም የግብጽን ሥልጣኔ የመሰረቱት ኢትዮጵያውያን ነበሩ፡፡ (እባክዎ የታሪክ አዋቂዎች የነበሩ ሁለት ግሪካውያን /ሄሮዱተስ 490-425 ዓ.ዓ እና ዲዮዶሩስ 60 ዓ.ዓ/ የጻፏቸውን መጻህፍት ያንብቡ፤ኢትዮጵያውያን የግብጽ ሥልጣኔ መስራቾች መሆናቸውን ይገነዘባሉ፡፡ በተጨማሪም ጉግል ውስጥ ገብተው "History of Ethiopia according to Herodutus, Diodoros and Strabo" የሚሰውን ይመልከቱ፡፡)

አሌክሳንደር ደቡባዊ ግብጽን ሰመውረር በመጣበት ወቅት ኢትዮጵያዊው ንጉሠ-ነገሥት አፄ ዋዜባ ጦሩን እንቀሳቅሶ ወደ ደቡባዊ ግብጽ የዘመተው ወረራውን ሰመቀልበስ ነበር እንጂ የስጋ ዘመዱና እንዲሁም የግብፅና የኑቢያ ንግሥት የነበረችውን ዳግማዊት ቅንዳቂስ ህንደኬን ሰመቀናቀን አልነበረም፡፡ ግብፃውያን አሌክሳንደርን እንደ ንጉሣቸው አልተቀበሉትም፡፡ ዳግማዊት ቅንዳቅስ አሌክሳንደርን አገባችና ክሥጋ ዘመድዋ ከአፄ ዋዜባ ጋር አስታረቀችው፡፡ በዚያን ወቅት የኢትዮጵያ ግዛት የነበረውን ሰሜናዊ ግብፅን አስካልነካብን ድረስ ደቡብ ግብፅን ቢይዝ ምን ችገረህ ብላ ዘመድዋን አግባባችው፡፡ ከዚያም በሁዋላ አሌክሳንደሪያ ተብላ በስሙ በተጠራችው በራቂዲ ክተማ ሰአሌክሳንደር የኢትዮጵያን ዘውድ ደፋችለትና አነገሠችው፡፡ ክዚህ በሁዋላ ነው እንግዲህ ግብፆች አሌክሳንደርን እነደ ንጉሣቸው የተቀበሉት፡፡(25) እንደ ሕዝብ በመኖርም ሆነ በሥልጣኔ እኛ ከግሪኮች የትየለሌ እንቀድማለን፡፡ ስለዚህ ግሪኮች ሰኛ ስም ሊያወጡልን ከቶ



የኦሮሞ እና የአማራ እውነተኛው የዘር ሐረግ ምንጭ ፍቅሬ ቶሎሳ

አይችሉም፡፡ ‹‹ኢትዮጵያውያን›› ያሉን እነሱ ከሆኑ ከዚያ በፊት ራሳችንን ማን ብለን እንጠራ ነበር? ‹‹ኢትዮጵያ›› የግሪክ ቃል ሳይሆን የኛ የራሳችን ነው፡፡ ራሳችንን ‹‹ኢትዮጵያውያኖች›› ብለን ስንጠራ ግሪኮች ሰምተው መልሰው በዚያው ጠሩን፡፡ ምናልባት ክግሪኮች ጋር ግንኙነት የፈጠሩ የመጀመሪያዎቹ ጥቂር ህዝቦች ኢትዮጵያውያኖች ሳይሆኑ አይቀርም፤ ከዚያ በሁዋላ ያገኙትን ጥቁር ሁሉ ‹‹ኢትዮጵያ›› እያሉ መጥራት የጀመሩ ይመስላል፡፡

ከላይ ያሰውን ሃሳብ በቀላሉ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ በስትሮንግ የተዘጋጀውን የግሪክን መዝገበ-ቃላት እንመልከት፤(26) "ኢትዮጵያ" የግሪክ ቃል ክሆነ በተነገረን መሰረት ‹‹ፊቱ በፀሃይ የተቃጠለ›› ከሚሰው ፍችው ጋር በግሪክ መዝገበ-ቃላት ውስጥ መገኘት አለበት፡፡ በግሪክ በፀሃይ የተቃጠለ ማለት ‹‹ካውማትዲዞ (kawmatdizo)›› ነው፡፡ ‹‹ፊት›› ማለት ደግሞ ‹‹ፔሪካሉፕቶ (perikalupto)›› ነው፡፡ ስለዚህ በግሪክ ‹‹ፊቱ የተቃጠለ›› ማለት ‹‹ካውማትዲዞ-ፔሪካሉፕቶ›› ነው፡፡ (strong`s Greek Lexicon,p.239 and p.4020) በዚህ ሁኔታ "ኢትዮጵያ" የሚሰው ቃል ‹‹ካውማትዲዞ-ፔሪካሉፕቶ›› መሆን ነበረበት፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያንም ‹‹ካውማትዲዞ ፔሪካሉፕቶኢያንስ›› ተብለን መጠራት ነበረብን ማለት ነው፡፡ ግሪክ ‹‹ኢትዮጵያ›› ብላ ሰየመችን ብሎ ማሰብ ምን ያህል አሳፋሪ እንደሆነ እዩ! ፍፁም ሃሰት ነው፡፡

ሌላው ክርክር በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ "ኢትዮጵያ" የሚሰው ቃል ‹‹ኩሽ››ን ተኪ ነው የሚሰው ነው፡፡(27) ኩሽ በጾታው ተባዕታይ ሲሆን ኢትዮጵያ ግን በእንስታይ ጾታ ነው የምትነገረው፡፡ ንጉሥ ዳዊት በመዝሙሩ ላይ ኢትዮጵያን እንደ ኩሽ በ‹‹ተባዕታይ ጾታ›› አልጠራትም፡፡ ‹‹ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች››(መዝሙር 68፡31) አለ እንጂ ‹‹ኩሽ እጁን ወደ ግዚአብሔር ይዘረጋል›› አላለም፡፡ "ኢትየጵያ" እና ‹‹ኩሽ›› በሚሉት ቃላት ላይ ብንከራከር እንኳዋ በዚህ ትንቢት ‹‹እሷ›› በሚሰው ሃሳብ ላይ ግን ልንከራከር አንችልም፡፡ ማንም እንደሚስማማበት በዚህ ትንቢት ውስጥ ተውላጠ-ስሙ ‹‹እሷ›› ነው እንጂ ‹‹እሱ›› አይደለም፡፡ ሌሎች ተጨማሪ ምሳሌዎችን መጥቀስ ቢቻልም ለመነሻ በዚህ ሳብቃ፡፡

ኤትኤል፣ "ኢትዮጵ" የሚል መለኮታዊ ስም ከወጣለት በሁዋላ ከኢየሩሳሌም ወደ ኩሻዊቷ ምድር አሁን ‹‹ኢትዮጵያ›› ተብላ ወደምትጠራዋ አገር የመጣበት ምክንያት እንደሚከተለው ነው። በርግጥ አመጣጡ ተልዕኮ ነበረው።

አክሱማይ ሲራክ በተባለው ከአንድ ሺ ዓመት በፊት በነበረው የታሪክ ሰው በተላለፈልን፣ እንዲሁም የአንዳ-ቤቱ ዘግዱር አማካኝነት በደረሱን ከሦስት ሺ ዐመታት በላይ ባስቆጠሩት ጽሁፎች (28) ውስጥ በተለይም በ *መጽሐፈ- ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ* የጥንት ታሪካችን መረጃ መሰረት ሁለቱም፣ ኦሮሞም አማራም፣ እንዲሁም ሁሉም ኢትዮጵያውያን የአንድ አባትና እናት ልጆች ናቸው። ያ የጥንት አባታችን መልከጼዴቅ ይባላል። እርሱም የሰላምና የጽድቅ ንጉሥ፣ እንዲሁም በምድሪቱ ላይ ከፍተኛው የእግዚአብሔር ካሕን የነበረ፣ ኢየሩሳሌምን የገነባ፣ አብርሃምና ሌሎችም ነገሥታት ጎንበስ ብለው እጅ የነሱት እና ምርቃቱን ለማግኘት ዓሥራት የገበሩለት ሰው ነው። (ዕብ. 7፡127) የእሱ ሚስት እናታችን ሳሌም ነበረች። አባታችን የአሳደጋትን ከተማ ለእናታችን መታሰቢያ ሳሌም ወይም እየሩሳሌም አላት። ሰማያዊ ሰላም ማለት ነው። ይህ አፈ-ታሪክ አይደለም፤ ተረትም አይደለም። የተመዘገበ እውነተኛ ታሪክ እንጂ።

ከእየሱስ ክርስቶስ ልደት 2000 ዓመት በፊት (አሁን ከ4000 ዓመት በፊት ማለት ነው) እግዚአብሔር መልከጼዴቅን አንድ ትዕዛዝ አዘዘው። ይኸውም ልጁን ኢትኤልን ቆየት ብሎ በእግዚአብሔር በራሱ ኢትዮጵ የተባለውን የዓባይ ወንዝ ምንጭ ወደ ሆነው ወደ ጣና ደሴት ሄዶ ይሰፍር ዘንድ እንዲልከው ነበር። ‹‹ኢትኤል›› ማለት ‹‹የእግዚአብሔር ስጦታ›› ማለት ነው።

እግዚአብሔር ኢትኤልን ወደ ኢትዮጵያ ሲልከው እግዚአብሔር ወልድ (እየሱስ ክርስቶስ፣ መሲሕ፣ ሙስሊሞች ደግሞ ኢሣ፣ ነቢይ የሚሉት) ከ2000 ዓመት በሁዋላ ሰው ሆኖ በቤተልሔም ሲወለድ የኢትኤል ዝርያዎችን ወደ ቤተልሔም ሲመራቸው በኢትዮጵያ በሚወጣው ኮከብ እየተመሩ የኢትዮጵያን ስጦታ ቢጫ ወርቅ፣ ከርቤና እጣን እንደሚያመጡለት አስቀደሞ ሲያመለክት ነው። በዚሁ መሰረት ኢቴኤል በዚያን ጊዜ የኩሽ ምድር ወደ ምትባለው ወደ ኢትዮጵያ መጣና ዛሬ ጎጃም በሚባለው ቦታ ሰፈረ። እግዚአብሔርም ስሙን





ከኢትኤል ወደ ኢትዮጵ ቀየረለት። ትርጉሙም ‹‹ለእግዚአብሔር የቢጫ ወርቅ ስጦታ›› ማለት ነው። በዚህም ኢትኤል "ኢትዮጵ" መባሉ ብቻ ሳይሆን የሰፈረባት ምድርም "ኢትዮጵያ" ትባል ጀመር። ከ2000 ዓመታተት በሁዋላ የኢትዮጵ ተወላጆች በዚያን ጊዜዋ የኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ 12 ንጉሦች ሆኑ። እግዚአብሔር እንዳለው እየሱስ ክርስቶስ ሲወለድ ስጦታ ለማበርከት ኮከቡ እየመራቸው ወደ ቤተልሄም አቀኑ።(29 )

አስራ ሁለቱም ንጉሶች አማራን፣ ኦሮሞን፣ አፋርን፣ ሶማሊን፣ ሐዲያን፣ እና ትግሬን ጨምሮ የኢትዮጵያን የተለያዩ ነገዶችን ይወክላሉ። አማራን የወከሉ ንጉሶች አቦል፣ ጦና፣ በረካ (እነዚህ ሶስቱ አቦል፣ ጦና እና በረካ የሚባሉት የተፈላ ቡና ደረጃዎችን ይጠቅሳሉ) እና አጎድጃ ጃቦን ይባላሉ። በጣና ሐይቅ ደሴት እና በተቀሩት የጎጃም አካባቢዎች ነበሩ። ንጉሥ መጋል የኦሮሞን ብሔር ይወክላሉ። የደርዲ እና፣ የሰገል፣ የማጂ እና የኦሮሞ ንጉሥ ነበሩ። እኝህ ታላቅ ንጉሥ እየሱስ ክርስቶስ ከመወለዱ ከ20 ዐመታት በፊት የመደባይ ኦሮሞን ካህናትና የኦሮሞን ሰራዊት ክተት ብለው ይዘው በዛን ጊዜ በመርከብ ሥራ ስመ-ጥር በነበሩት በአፋር ባለእጆች በተበጁ አስደናቂ መርከቦች ወደ ፖርቱጋል እና ስፔን ቀዝፈው ነበር። የጉዞአቸው ዓላማ እነዚህን አገሮች ለማስገበር እና ቅኝ ለመግዛት ነበር። (30) እቅዳቸውም በወቅቱ ተሳክቶላቸዋል። እዛ ከደረሱም በሁዋላ አፋር ውስጥ የነበረችውን የባህር ዳር ተርሴስን ለማስታወስ የእስፔንን ባህር ዳር ተርሴስ ብለው ሰይመዋታል። እስከ ዛሬም ድረስ ተርሴስ ትባላለች። በርግጥም ስፔን ውስጥ ያለችው ተርሴስ ወይም ታርሲስ ስምዋ ኢትዮጵያ ውስጥ በአፋር ከነበረችው ታርሲስ ወይም ተርሴስ ጋር ተመሳሳይ ነው። እቅጩን ለመናገር ንጉሥ ዳዊት በመዝሙር ላይ (31) የተርሴስ (አፋር ውስጥ) እና የደሴት ነገሥታት ስጦታ (ለእየሱስ) ያመጣሉ ይላል። ከተተነበየ ከአንድ ሺ ዓመት በሁዋላ የተፈፀመ ትንቢት ነው። ከ12ቱ ንጉሦች አንዱ የአፋር ግዛትን የሚወክለው ሙርኖ አፊር የተሰኘውን የአፋርን ወርቅ ከተርሴስ ይዞ ወደ ቤተ-ልሔም ተጉዟል። (32) ፖርቱጋል ሲባል ‹‹ፖርት-ጋል›› ማለትም ‹‹ፖርት ጋላ፤ የጋላ ወደብ›› ለማለት ይሆናል እያልኩ እመራመራለሁ። በዚያን ወቅት ‹‹ጋላ›› የሚለው ቃል አሉታዊ ትርጉም አልነበረውም። ጥበበ-እውቀትን እና ጠቢብነትን ነበር

የሚያመለከተው:: የሆነው ሆኖ ኦሮሞ ከስፔን እና ከፖርቱጋል ጋ
የሆነ ግንኙነት እንደነበረው ‹‹ሴፎራ›› (በኦሮምኛው አጠራር ሰጲራ
የሚለው ቃል ያመለክታል:: እነዚህ የስፔንና የፖርቱጋል ስም
በኢንተርኔት ላይም ይገኛሉ:: አባ ባሕርይ እንደ ዘገቡት የቦረና አባ
ሰጲራ ነው:: (33) የቦረና አባት የፖርቱጋል ወይም የስፔን ስ
የሚኖረው በምን ታምር ነው? Huntingford ለዚህ ጥያቄ የሚሰጠ
መልስ ይህ ነው:-

*"ጋሎች (በኢትዮጵያ ውስጥ) ድል ከተቀዳጁ በኋላ ሁለ*
*ፖርቹጋሎች እናርያ መጥተው ተቀመጡ:: የግራኝ ወረራን ለመቀልበ*
*ገላውዲዎስን ሊረዳ የመጣውን ጦር ከመራው ከክሪስቶፎር ዳጋማ ጋ*
*ወደ አቢሲኒያ የመጡ ሲሆኑ በባሕላዊው አጠራር ሲጺራ እና ሳጽየ*
*ተባሉ:: ሁለተኛው የጋላ ሴት አግብቶ ምናልባትም በእናሪያ የሆ*
*ሹመት ሳይሰጠው አልቀረም:: በ19ነኛው ክፍለ-ዘመን የተነሱ ንጉሦ*
*የሱ (የሳጽየራ) ዝርያ ነን ብለው የማዕረግ ስማቸውንም "ሞቲ" እ*
*"ንጉስ" ከሚሉት "ሱጼራ" ወደሚለው ቀይረዋል::"* (34)

ኢትዮጵ ሲና ከተባለችውና በሁዋላ እንቆጳግዮን (የግዮ
ቢጫወርቅጌጥ) ተብላ ከተጠራችው ሚስቱ አሥር ወንዶችንና ሶስት
ሴቶችን ወልዷል:: ይኸውም ባልና ሚስቱ በ‹‹ቢጫ ወርቅ›› በተሞላው
በግዮን ወንዝ መነሻ ላይ ከሰፈሩ በሁዋላ ነው:: ወንዶቹ ልጆች ፤አቲባ
ቢኦር፥ ተምና፥ አቴር፥ አሻን፥ አክዚብ፥ በሪሳ፥ ቴስቢ፥ ቶላ፥ እና አዜብ
ይባላሉ:: (35)

የሴቶቹ ስም ሎዛ፤ ሚልካ እና ሱባ ናቸው:: ከኢትዮጵ ወንዶች ልጆች
አንዱ አላይ እንደ ሰፈረው ቶላ ይባላል:: የሚገርመኝ ነገር፥ በወለጋ
የኦሮሞው አባቴ ወንድም፥ የኔ አጎት ስም ቶላ ነበር:: ኢትዮጵ እና
ልጁ ቶላ ከኦሮሞዎች ጋር አንድ አይነት ግንኙነት እና ትስስር
እንዳለው ይህ ክስተት ይጠቁመኛል:: በአጋጣሚም እንዳልሆነ
ይነግረኛል:: ሌላው የሚደንቀኝ ነገር ሁለተኛው የኢትዮጵ ልጅ ተስቢ
መባሉና ተስቢያው ኤልያስ የሱ ተወላጅ መሆኑ ነው:: በእስራኤል
የእስራኤላውያን ነብይ ሆኖ ሲኖር እግዚአብሔር በአጸደ ሥጋ እያለ
በእሳት ሰረገላ ወደ ሰማይ ነጠቀው:: ወይም አመጠቀው:: ይህ ሞትን
ሳያይ በህይወት የሚኖር እጅግ ታላቅ ነቢይ ከአባታችን ከኢትዮጵ
የወረደ የኛ ወገን በመሆኑ ሁላችንም ኢትዮጵያውያን ልንኮራ ይገባል::





የእግዚአብሄር ሰው ኢዮብም የኛው ወገን ነበር እንጂ እስራኤላዊ አልበረም:: የእሱን የህይወት ታሪክ እስራኤላውያን በመፅሃፍ ቅዱሳቸው ውስጥ ከተቱት እንጂ:: እሱም ከመልከፀዲቅ ወርዶ በእስራኤል ሲኖር ነበር ሰይጣን በእሱ ላይ ከእግዚአብሄር ተወራርዶ፥ እግዚአብሄርን አስፈቅዶ የተፈታተነው:: ኢትዮጵ ዘመዱን ለማስታወስ "ኢትዮጵ" ተብሎ ተጠራ:: በልማዳዊ አጠራር "ኢትዮጵ" ከሚለው ቃል ውስጥ "ት" ን ጥለው እና "ጵ" ን "ብ" ብለው "እዮብ" አሉት:: መባል የነበረበት ግን "ኢትዮጵ" ነው:: ሰይጣን ልጆቹን ገድሎበት እግዚአብሄር እንደገና 10 ወንዶች ልጆች ሰጥቶ ከካሰው በሁዋላ አስሩም ልጆች ወደ ኢትዮጵያ አፋር ግዛት መጥተው ከኢትዮጵያውያን ዘመዶቻቸው ጋር ተቀላቅለው እዛው መቅረታቸውን ታሪካችን ይዘግባል:: እዮብ ዘመዳችን ባይሆን ኖሮ ልጆቹ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ባልኖሩ ነበር:: አስሩ የኢትዮጵ ወንዶች ልጆችና ልጆቻቸው እጅግ ብዙ ጎሳዎችና ነገዶች ሆነው የሁሉም ኢትዮጵያውያን አባትና እናት ሆነዋል:: ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን ሕዝቦች ሁሉ አስገኝተው ሁላችንንም አዛምደውናል:: ሁላችንም የአንድ አባት እና እናት ልጆች ስለሆንን ደስ እንድንሰኝ ይገባል::